# በቱለማ ኦሮሞ ገዳ ሥርዓት እንስትነትን የሚገልፁ የከበሩ ንዋያት ትዕምርታዊ ጥናት[1]

ገናናው ከተማ[2] እና ታደሰ በሪሶ[3]

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በቱለማ ኦሮሞ ገዳ ሥርዓት እንስትነትን የሚያመለክቱ ትዕምርቶችን በትንታኔ ማሳየት ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት የከበሩ ንዋያት የቱለማ ኦሮሞን ባህል እና ወግ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከዚህ በፊት በተለይም ከእንስትነት እና ከትዕምርት ብሎም ከሥርዓተ ከበራ አንፃር አልተጠኑም፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ ምርምርን የተከተለ ሲሆን፣ ገላጭ የአጠናን ስልትን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ በቃለ መጠይቅ፣ በመስክ ምልከታ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተሰበሰቡ ቀዳማይ መረጃዎች ከልዩ ልዩ ስነዘዴዎች፣ ፅንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች ጋር ተዋህደው ተተንትነዋል፡፡ መረጃዎቹ ስለ ጫጬ፣ ጨሌ፣ ሲንቄ እና ተያያዥ ጉዳዮች የሚያወሱ ናቸው፡፡ በትንታኔው እንደታየውም በገዳ ሥርዓት ውስጥ ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው እነዚህ እንስትነትን የሚያመለክቱት የከበሩ ንዋያት ባላቸው ትዕምርታዊ ፍቺ የሴቶችን ማህበራዊ ደረጃ እና ሚና፣ ክብር፣ ተቀባይነት እና ተደማጭነትን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ከትዕምርታዊ ፍቺ አንፃር ደግሞ እንስትነትን እና መራባትን የሚገልፁ ሲሆን ዕርቅ ለመፈፀም እና ግጭቶችን ለማስወገድ ጉልህ ድርሻ ያላቸው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

**የጥናቱ ቁልፍ ቃላት፡-** [እንስትነት፣ ትዕምርት፣ ጫጬ፣ ጨሌ፣ ሲንቄ]፡፡

## 1. መግቢያ

ፎክሎር (folklore) የተሰኘው የእንግሊዝኛ ቃል የፎክ (folk) እና ሎር (lore) ድምር ውጤት ነው፡፡ የአንድ ህዝብ ወይም ቡድን የጋራ ፈጠራ እና ጥበብ፣ ዕውቀት፣ ፍልስፍና፣ የኑሮ ዘዴ፣ እምነት፣ እሴት፣ ወግ እና ልማድ፣ ህግና ደንብ፣ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍ እና ስነጥበብ፣ ሙዚቃ፣ ባህላዊ ጭፈራ፣ ሚት (myth)፣ ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ልማዶች፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ቁሳዊ ባህል፣ ትዕምርት (Symbol)፡- ሀገረሰባዊ ውክልና፣ ቀለም፣ ቁጥር፣ ሀገረሰባዊ ትዕምርት፣ ምልክት፣ ሀገረሰባዊ ስም እና ሕዝባዊ ቦታ፣ ሥርዓተ ከበራ ወዘተ. የሚጠኑበት የማህበራዊ ሳይንስ አካል ነው (Dorson, 1972፤ ፈቃደ 1991 ዓ.ም[4]፤ ሰለሞን 2007ዓ.ም)፡፡

---

[1] ይህ መጣጥፍ (Article) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር በፎክሎር ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያነት በ2014 ዓ.ም ከተካሄደ ጥናት ለዚሁ ተግባር በሚስማማ መልኩ የቀረበ ነው፡፡

[2] በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ እጩ ተመራቂ፡፡ genanawkt@gmail.com

[3] ተባባሪ ፕሮፌሰር፤ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ taddesse.berisso@aau.edu.et

[4] "ዓ.ም." ይህ ምህፃረ ቃል ያላቸው እንደ ኢትዮጵያ፤ የሌላቸው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር የቀረቡ ናቸው፡፡

በተዘረዘሩት የፎክሎር ዘርፎች ውስጥ ከተካተቱት መካከል ቁሳዊ ባህል አንዱ ሲሆን ከዚሁ ዘርፍ ጋር ቅርበት ያላቸው፡- ትዕምርት፣ ሀገረሰባዊ ውክልና፣ ሀገረሰባዊ ትዕምርት፣ ምልክት የተሰኙ ቃላት ይገኙበታል፡፡ እነዚህ የትዕምርት እና የምልክት ዓይነቶች ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላላቸው ለጥናቱ መመልከቻነት አገልግለዋል፡፡

ትዕምርቶቹ እና ምልክቶቹ በዓይነትም በቅርፅም ብዙ ቢሆኑም እንኳ በቱለማ ኦሮሞ[5] ገዳ ሥርዓት እንስትነትን[6] የሚገልፁ የከበሩ ንዋያት[7] በሚል ርዕስ የቀረበው ይህ መጣጥፍ ትዕምርታዊ ትንተና የሚሰጥ ነው፡፡ የከበሩ ንዋያቱ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን ለክብራቸውም የህግ ድንጋጌ የተሰጣቸው ናቸው፡፡ የገዳ ሥርዓት ህግ በውስጡ ከያዛቸው አያሌ ጉዳዮች መካከል የሴቶችን መብት፣ እኩልነት እና ክብር የሚመለከተው ክፍል ተጠቃሽ ነው፡፡[8] የሴቶች መብት በገዳ ህግ ይከበራል፤ ይጠበቃልም፡፡ የሴቶችን ሁለንተናዊ መብቶች የሚገልፀው ይህ ህግ "የሴቶች መብት ህግ/ Seera mirga dubartii" በሚል ጥቅል ስያሜው የሚታወቅ ሲሆን ከእንስቷ የራስ ፀጉር ጀምሮ ማህበራዊ መብቶቿን ጭምር አካቶ የያዘ ነው፣

> *ሴረ ሚርገ ዱበርቲ (Seera mirga dubartii):- ይህ የሴቶችን መብት የሚመለከት ደንብ ነው፡፡ በዚህ ሥር ከሚደነገጉት ደንቦች ውስጥ የሚከተሉትን ለአብነት መጥቀሱ ለግንዛቤ ሊረዳ ይችላል፡፡ ሴረ ቀጂሣ ዱበርቲ (Seera Qajjiisa dubartii) - "ቀጂሣ ዱበርቲ" የሚለው የሴት ፀጉር ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በጨፌው ላይ በተደነገገው መሠረት ከሴት ጋር ተጣልቶ ፀጉሯን መንቀል አይቻልም ወይም አይፈቀድም፡፡ እንደ አገር ሽማግሌዎች ወይም አባገዳዎች አባባል የሴትን ፀጉር የነቀለ እንደ "ፈልፈላ"[9] ይታያል፡፡ በዚህ ጥፋቱ ከተጠያቂነት አያመልጥም፡፡ እንደ ነፍሰ ገዳይ ተቆጥሮ ግማሽ*

---

[5] የቱለማ ኦሮሞ በሀገሪቱ እምብርት ወይም በማዕከላዊ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል (የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ 1998፡ 140)፡፡

[6] 'እንስትነት' ፡- 'እንስት' ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን 'እንስት' የአማርኛው 'ሴት' ፤ እንስትነት ደግሞ 'የሴትነት' አቻ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከነዚሁ ቃላት የተመዘዘው 'ሴታዊነት' የእንግሊዘኛውን "ፌሚኒዝም/ Feminism" ይወክላል፡፡ ቃሉም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተለመደ መጥቷል፡፡

[7] በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት የከበሩ ንዋያት በተናጥል "የከበረ ንዋይ/ Ulfaa"፣ በወል "Ulfaalee/ የከበሩ ንዋያት" ይሰኛሉ፣ "የከበረ ንዋይ ማለት የከበረ ከሚለው ቃል የመጣ ነው፡፡ የከበረ የተባለውም በኦሮሞ ዘንድ ክብር ስላለው ነው፡፡ የቱለማ ምክር ቤት (ጨፌ) የከበረ ንዋይ (ክቡር) ነው በማለት አዋጅ ያስነገረለት አለ፡፡ ቦኩ ክቡር (የተከበረ) ነው፣ ከለቻ ክቡር ነው፣ ሜጬ ክቡር ነው... የቱለማ ምክር ቤት እውቅና የሰጣቸው ናቸው" (አቶ ማሞ ገዳ፣ 08/12/2011 ዓ.ም አዳማ - በትርጉም የቀረበ)፡፡ እንዲህም በመሆኑ የከበረ ንዋይ 'ቁስ' ወይም 'ዕቃ' (Meeshaa, mi'a) ተብሎ አይጠራም፤ ጥናቱም ይህንኑ የኅብረተሰቡን አገላለፅ ተጠቅሟል፡፡

[8] "ወንድና ሴትን እኩል የሚያደርግ ሥርዓት የገዳ ሥርዓት ነው፡፡ ሚስት የሌለው ሰው አባ ገዳ መሆን አይችልም፡፡ አባ ቦኩም ሚስት ሊኖረው ይገባል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሁለቱም ሰዎች (ወንድና ሴት) የከበሩ ናቸው፤ ሁለቱም ክቡራን ናቸው" (አቶ ቡላ ሀዬ፣ 11/01/2012 ዓ.ም መቂ - በትርጉም የቀረበ)፡፡

[9] "ፈልፈላ /falfalaa" ሟርተኛ ማለት ነው (ሙልጌታ 1997ዓ.ም፡ 24)፡፡ ክፉ ነገር የሚያስብ እና የሚያደርግ ሰው እንደማለት ይሆናል፡፡

*ጉማ እንዲቀጣ በሴረ ጉማ ውስጥ መደንገጉን የአገር ሽማግሌዎች ያስረዳሉ (ሙልጌታ፣ 1997ዓ.ም፡ 23-24)፡፡*

ሙልጌታ (1997ዓ.ም)፣ "የወላድ ህግ - ሴረ ኢላንሶ/ Seera illaansoo" እና "የሴት መሐረብ ህግ - ሴረ ሀቅጡ ዱበርቲ/ Seera haqxuu dubartii" የተሰኙትን ሀረጋትም አብራርተዋል፡፡ በሴረ ኢላንሶ መሠረት ልትወልድ የደረሰችን ነብሰጡር ወይም ምጥ የያዛትን ሴት በሰላም ሳትገላገል (ሳትወልድ) ትቶ መሄድ እንዲሁም በሴረ ሃቅጡ ዱበርቲ ደግሞ የጤንነቷ፣ የውበቷ እና የግል ንብረቷ መገለጫ የሆነውን የእንስቷን መሐረብ በግድ ወይም በጉልበት አስገድዶ መውሰድ በገዳ ህግ የሚያስቀጣ ነው (ሙልጌታ 1997ዓ.ም፡ 24)።

የገዳ ሥርዓት ህግ ከተጠቀሱት የሴቶች ሙብት በተጨማሪም ከእንስትነት ወይም ከሥርዓተ ፆታ ጋር የተያያዙ ሌሎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሙብቶችን ያካተተ ሲሆን የተወሰኑት በዚህ ጥናት የተለያዩ ንዑሳን ርዕሶች ውስጥ ታይተዋል፡፡

ከገዳ ሥርዓት እና ህግ ባሻገር የተለያዩ ሴት ንግሥታት የኦሮሞን ህዝብ እንዳስተዳደሩ በአፈ ታሪክ ይነገራል፡፡[10] ከነዚህም እንስቶች መካከል አንዷ አኮ መኖዬ (Akkoo Manooyyee) ናት፡፡ በኦሮሞ ታሪክ ውስጥ የገነነ ስም ነበራት፤ ትዕዛዞቿም በእጅጉ የከበዱ ነበሩ፡፡ ሰማይም ምድርም ሳይነካ - በሰማይ እና በምድር መካከል ቤት ስሩልኝ በማለት በሰው ልጅ የማይፈፀሙ ትዕዛዛትን ስታዝ እንደነበር ስለ አኮ መኖዬ የሚያወሳው የአፋን ኦሮሞ አፈ ታሪክ ያስረዳል፡፡ በአኮ መኖዬ ዘመን የወንዶች የበላይነት አክትሞ ነበር ይባላል (Dirribii, 2016: 191-192; Gananawu, 2004፡ 20)። የወንዶችን የበላይነት በመቃወም እና በመታገል ረገድ ከኦሮሞ ታሪክ ባለፈም በኢትዮጵያ

[10] Dirribii (2016፡ 191-192) በጥንታዊው የእማሆይ አስተዳደር (Bulchiinsa Dubartii) ዘመን አምስት የኦሮሞ እንስት ንግሥታት እንደነበሩ ገልፀዋል፡፡ እነሱም፡- 1. Mootittii Maccaa - Haadha Sonkooroo - የመጫ ንግሥት - ሀደ' ሰንኮሮ፣ 2. Mootittii Tuulamaa - Akkoo Manooyyee - የቱለማ ንግሥት - አኮ መኖዬ፣ 3. Mootittii Ituu-Humbannaa - mootee Qorkee- የኢቱ ሁምበና ንግሥት ሞቴ ቆርኬ፣ 4. Mootittii Booranaa - Haadha Abanooyyee- የቦረና ንግሥት - ሀደ' አበኖዬ፣ 5. Mootittii karrayyuu - Akkoo Manooyyee የከረዩ ንግሥት - አኮ መኖዬ ናቸው፡፡ የጉጂ ኦሮሞ ደግሞ አራት ንግሥታት እንደነበሩት በመጽሐፉ የተመለከቱ ሲሆን 1. Akkoo Qarooyyee Garooyyee - አኮ ቀሮዬ፣ ገሮዬ፣ 2. Akkoo Lasii Lasooyyee - አኮ ለሲ ለሶዬ 3. Akkoo Qadhoo Qasooyyee fi – አኮ ቀዶ' ቀሶዬ እና 4. Akkoo Manooyyee Jedhamu- አኮ መኖዬ ይባላሉ፡፡ እነዚህ ንግሥታት በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ የየራሳቸው አፈ ታሪክ ያላቸው ሲሆን፣ ይበልጥ ታዋቂነት ያላት አኮ መኖዬ ናት፡፡

ምናልባትም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ[11] የመጀመሪያዋ የሴታዊነት (feminism[12]) ንቅናቄ አራማጅ እንደነበረች ይገመታል፡፡ ለሴቶች መብት ትግል መነሻ ፋና ወጊ የሆነችው አኮ መኖዬ የሴቶች ታሪክ እምብዛም በማይታወቅበት ዘመን የወንዶችን ዓለም ጥሳ የወጣች ሲሆን፣ በዘመኗም ተፅዕኖ ፈጣሪ እንደነበረች ይነገራል፡፡ በገዳ ሥርዓትም ሆነ በኦሮሞ ታሪክ ውስጥ ከሚስተዋለው ከዚሁ የሴቶች መብት ትግል እና ታሪካዊ ድርሻ በተጨማሪ የሴቶችን ክብር የሚገልፁ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ፣ ባህላዊ እና ትውፊታዊ እሴቶች አያሌ ናቸው፡፡

ከነዚህም መካከል የጥናቱ ዋና ትኩረት እና መዳረሻ የሆኑት የከበሩ ንዋያት ወይም የእንስትነት ትዕምርቶች የሆኑት ጫጬ፣ ጨሌ፣ ሲንቄ እና ተያያዥ ጉዳዮች ተተንትነዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲው ቤተመጻሕፍት እና አርካይቭ ክፍል ባደረግነው የካልዓይ መረጃ ፍተሻ በተዘዋዋሪ ካልሆነ በቀር ከቱለማ ኦሮሞ ገዳ ሥርዓት እንስትነትን የሚገልፁ የከበሩ ንዋያት ትዕምርቶች አንፃር የተሰራ የፎክሎር ጥናት አለማግኘታችን እንዲሁም ትዕምርት በሀገር ዓቀፍ ደረጃም ቢሆን የፎክሎር ጥናት እምብዛም ያልተሰራበት ከመሆኑ የተነሳ በዚህ ረገድ የታየውን የእውቀት ክፍተት ሊሞላ ይችላል የሚል ግምት አለን፡፡ ይኸውም የምርምሩ አነሳሽ ምክንያት ለዚህ መጣጥፍ ዝግጅትም ትኩረታችንን ስለሳበ እራሱን ችሎ በዚህ መልክ ቀርቧል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በቱለማ ኦሮሞ ገዳ ሥርዓት እንስትነትን የሚያመለክቱ የከበሩ ንዋያት ትዕምርታዊ ይዘት በትንተና ማሳየት ነው፡፡ ዝርዝር ዓላማዎችም አሉት፡፡ እነርሱም፡- የእንስትነት ትዕምርቶችን ዓይነት እና ውክልና ማብራራት፣ ትዕምርቶቹ በከበራ ውስጥ ያላቸውን ሚና ማሳየት፣ ለኅብረተሰቡም የሚሰጡትን ሁለንተናዊ ጠቀሜታዎች መግለፅ የሚሉ ናቸው፡፡

ጥናቱ በቱለማ ገዳ ሥርዓት ውስጥ ከትዕምርት እና ምልክት አንፃር ሀደ ሲንቄ (Haadha Siinqee) ወይም እንስቶች የሚጠቀሙባቸውን የከበሩ ንዋያት፣ የፆታ እና የዕድሜ እርከን ምልክቶች እና ትዕምርታዊ ፍቺዎች፤ እነዚህም ትዕምርቶች በሥርዓተ ከበራ ውስጥ ያላቸውን ሚና በማሳየት ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ልዩ ቦታውን ከመወሰን አንፃር ደግሞ የከበሩ ንዋያቱን አሁንም እየተጠቀመበት ያለው የቱለማ ኦሮሞ በሚኖርበት አካባቢ ይበልጡንም የገዳ ሥርዓት እና የዋቄፈና እምነት

[11] በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከፆታ እኩልነት እና መብት ጋር በተያይዘ የሴቶች ንቅናቄ የተጀመረው በ19ኛው ክፍለ ዘመን ለዚያውም በቅርቡ እ.ኤ.አ በ1970ዎቹ እና በ1980ዎቹ ገደማ ነው (Hooks, 2015: 15)፡፡ የአኮ መኖዬ ዘመን በውል ያልታወቀ እና ጥንታዊ እንደሆነ ይነገራል፡፡ የአኮ መኖዬ ታሪክ በጽሑፍ ሰፍሮ የሚገኘው በአረብ ጸሐፊዎች አጠራር "ባኒ አል- ሃመዊያህ / Bani al-Hamwiyah በ10ኛው… ክፍለ ዘመን ገደማ የነበረች እና ጠንካራ ሠራዊት የነበራት እንደነበረች የታሪክ ሰነዶች ያስረዳሉ (Taddesse, 1972: 39)፡፡ በተመሳሳይ ብሩ (2008ዓ.ም፣ 307) "ኤል" የሚሰኘው የአረብኛ ቃል ሲገደፍ ቀሪው ሃመዊያ ዛሬም በመሀል ኢትዮጵያ ሰፍሮ ከሚገኘው የአመያ ኦሮሞ ጋር እንደሚቀራረብ እና በመላው የኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ የሚነገር የአንዲት አምባገነን መሪ ትውፊት ጋር የሚዛመድ መሆኑን የተለያዩ መረጃዎችን በማጣቀስ ያስረዳል፡፡ እሸቱ (2001ዓ.ም፡ 33) በበኩሉ፣ "በ10ኛው ምዕተ ዓመት ውስጥ በተፃፉ የክርስቲያኖች ነገሥታት ገድል ውስጥ ባዲት የምትባል ማያ የተባለ ኦሮሞ ሴት ልጅ እንደነበረች ይነገራል፡፡ በዚህ ማያ በተባለው ሰው ስም አንዱ የባቢሌ ጎሣ እንደሚጠራ አሁንም የሚታወቅ ነው" ብሏል፡፡ የአኮ መኖዬ/ አኮ ማያ ጉዳይ ተጨማሪ ጥናትን የሚጋብዝ ነው፡፡

[12] ሴታዊነት (Feminism) ሴቶች ከወንዶች እኩል መብት እና እድል እንዲኖራቸው የሚያልም፤ ይህም ዓላማ እንዲሳካ የሚታገል ነው - "Feminism the belief and aim that women shuld have the same right and opportunities as men: the struggle to achieve this aim" (Hornbay, 2010:545). ሴቶች ከወንዶች እኩል መብት እና እድል እንዲኖራቸው መታገል ብቻም ሳይሆን የሚደርስባቸውን (የደረሰባቸውን) በደል እና ጥቃት የሚቃወም ፖለቲካዊ ንቅናቄም ነው፡፡

በሚከወኑበት የከበራ ቦታዎች (ምሥራቅ ሸዋ) ላይ ያተኮረ ነው፡፡[13] ጥናቱ በቱለማ ኦሮሞ ገዳ ሥርዓት ውስጥ ከእንስትነት እና ከዕድሜ እርከን ጋር የተያያዙ ትዕምርቶችን ለመለየት ያስችላል፡፡ አቀራረቡም በየተለያዩ ንዑሳን ርዕሶች የተከፋፈለ ሲሆን ቀዳሚው የጥናቱን ስነዘዴ የተመለከተ ነው፡፡

## 2. የጥናቱ ዘዴዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች እና የአተናተን ዘዴዎችን ተከትሏል፡፡

### 2.1 የጥናቱ ዓይነት

በቱለማ ገዳ ሥርዓት ውስጥ ጉልህ ሚና ያላቸውን እንስትነትን የሚያመለክቱ ትዕምርቶችን ለማጥናት በመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ያገኘናቸውን የፎክሎር መረጃዎች ለመተንተን ዓይነታዊ የምርምር (Qualitative Research) ስልትን ተጠቅመናል፡፡ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥልቅ ገለፃ እና ትንታኔ የሚሰጥ ነው፡፡ የምርምር ዘዴው አንድን ጉዳይ ከመፈከር ወይም ከመተንተን ጋር በተያያዘ ለምሳሌ የቁሳዊ ባህልን፣ የትዕምርት እና የምልክትን ውክልና በገለፃ አጉልቶ ያሳያል፤ ይተነትናል (Mertens, 2015፡ 296)።

ይህም ዘዴ ስለ አንድ ጉዳይ በገለፃ መልክ በማቅረብ ግንዛቤ ለመፍጠር እና እውቀትን ለማስፋት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው (Mertens, 2015፡ 296)፡፡ ይኸውም "ዓይነታዊ ምርምር መረጃዎችን በቃላት የሚገለፅ ነው" (Walliman, 2006: 129)፡፡ በመሆኑም ገላጭ ስልትን በመጠቀም በቱለማ ኦሮሞ ገዳ ሥርዓት ውስጥ እንስትነትን የሚያመለክቱ ትዕምርቶችን ተንትነናል፡፡

### 2.2. የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ትዕምርቶቹን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሰበሰብናቸው መረጃዎች በሦስት የአጠናን ዘዴዎች ማለትም በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ውይይት እና በምልከታ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ከጥናቱ ዓይነት አንፃር "ዓይነታዊ ምርምር ሦስት የተለመዱ (የታወቁ) ዘዴዎችን ይጠቀማል። እነርሱም፡- ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት ናቸው" (Mack, 2005: 2)፡፡ ስለሆነም ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ መስከ በመውጣት እና ምልከታ በማድረግ በመቅረፀ ድምፅ፣ በቪዲዮ እና በፎቶግራፍ ካሜራ በመታገዝ መረጃዎችን በቃለ ምልልስ እና በከተተኳሪ የቡድን ውይይት ሰብስበናል፡፡

#### 2.2.1. ምልከታ

ከትዕምርት አንፃር ለተሰበሰቡት መረጃዎች ጥሩ ግንዛቤ ለማግኘት ያስችለን ዘንድ የገዳ ሥርዓት እና የዋቄፈና እምነት በሚከወንበት ሥፍራ በተለይም በቢሾፍቱ እና አካባቢዋ (የሦስቱ ቱለማዎች

[13] የገዳ ሥርዓት አወቃቀር ልክ እንደ መንግሥት አስተዳደር ሥርዓት የቀበሌ፣ የወረዳ እና የዞን አደረጃጀትን የማይከተል መሆኑን ልብ ይሏል። ስለሆነም የጥናቱ ወሰን ከቱለማ ገዳ አወቃቀር ጋር ተያይዞ የሚታይ ይሆናል።

የከበራ ማዕከላት) በመሄድ የሀደ’ ሲንቄዎችን (የእንስቶችን) አኗኗር፣ የህዝቡን የርስ በርስ ማኅበራዊ መስተጋብር እና በሥርዓተ ከበራ ወቅት የትዕምርቶቹን አጠቃቀም በማስመልከት ምልከታ አድርገናል፡፡ ለፎክሎር ጥናት መረጃን ለመሰበሰብ ከሚያስፈልጉ መቼቶች መካከል ተፈጥሯዊ የመቼት ዓይነትን በመጠቀም ስለትዕምርቶቹ ምንነት እና አተገባበር አስፈላጊውን መረጃ የሰበሰብን ሲሆን የተሳትፎ  እና ታዛቢ ምልከታም ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ በተሳትፎ ምልከታ ተመራማሪው ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆን ከማህበረሰቡ ጥሩ ልምድ እና ክሂሎት የሚጋራበት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ ይሁንና ተመራማሪው ትኩረቱ በተሳትፎው ላይ ስለሚሆን ረዳት ከሌለው ማስታወሻ መውሰድ ስለማይችል በመሐል ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ሊያመልጡት ይችላሉ (Mertens, 2015፡ 447)፡፡ ከቀረበው ሃሳብ አንፃር በታዛቢ ምልከታ የተሻለ እና ተጨባጭ መረጃ ማግኘት የሚቻል ቢሆንም ስለጉዳዩ ያለን ግንዛቤ እና ከኅብረተሰቡ ጋር የነበረን ቅርበት ውስንነት እንዳይኖረው በማሰብ ሁለቱንም ስልት በመደባለቅ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችለናል፡፡ በዚህ የምልከታ ዘዴ ከህብረተሰቡ ጋር በቆየንባቸው[14] ጊዜያት የከበሩ ንዋያቱን ስያሜ፣ አሰራራቸውን፣ ማህበራዊ ፍቺያቸውን፣ አገልግሎታቸውን እና በከበራ ወቅት ያለቸውን ሚና በማየት ለትንታኔው አውለናል።

### 2.2.2. ቃለ መጠይቅ እና የናሙና አመራረጥ

ቃለ መጠይቅ እንደ ምልከታ ባሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች ተደራሽ ያልሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት እና ለመሰብሰብ በእጅጉ ጠቃሚ የሆነ ዘዴ ነው (Mack et al, 2005; Bloor and Wood, 2006; Blaxter et al, 2006)፡፡ በዚህ መሰሉ ሂደት የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ዘዴ ወሳኝ ነው፡፡

“በዓይነታዊ የምርምር (Qualitative Research) ዓይነት፣ ተመራማሪው ከልምዱ በመነሳት መረጃ ይኖራቸዋል ብሎ የሚገምታቸውን ሰዎች በመምረጥ በጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል” (ያለው፤ 2006ዓ.ም፣19)፡፡ በዚህ ዘዴም ስለ ቱለማ ገዳ ሥርዓት እንስትነትን የሚያመለክቱ የከበሩ ንዋያትን አሰራር እና ትዕምርታዊ ፍቺያቸውን በደንብ ያውቃሉ የሚባሉ ሰዎችን (የባህሉ አዋቂዎችን) ማለትም ሀደ’  ሲንቄዎች፣ አባ ገዳዎች እና ሃዩዎች እና አዛውንቶች፣ በዕድሜ ገፋ ያሉ እናቶች፣ ወጣቶች፣ የቢሮ ሠራተኞች፣ የታሪክ መምህራን እንዲሁም የባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች፣ በአካባቢው ላይ ምርምር ያካሄዱ ምሁራን (አጥኚዎች) ስብጥሩን በጠበቀ ሁኔታ የመረጃ ምንጮቻችን ሆነዋል፡፡ ካሉት የእንስትነት መግለጫ የከበሩ ንዋያት ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸውን የጫጩ፣ ጨሌ፣ ሲንቄ እና ከነዚሁ የከበሩ ንዋያት ጋር ሳይነጣጠሉ በአንድነት የሚያዙትን ጋዲ፣ ኦኮሌ፣ ቀቤ፣ ጪጮ፣ ጋዮ እና ጡንጦ ርዕሰ ጉዳዮች ለማሳካት የተዘጋጁ ጥያቄዎችን በመደበኛ ጊዜ በማቅረብ ምላሽ እንዲሰጡም አድርገናል፡፡ ያልታቀዱ ጥያቄዎችንም በኢ-መደበኛ ጊዜ በመጠየቅ መረጃዎችን ሰብስበናል፡፡ የመረጃውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥም ለሀደ’ ሲንቄ፣ ለአባ ገዳ፣ ለአባ

---

[14] ይህን መጣጥፍ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከህብረተሰቡ ጋር የቆየንባቸው ቀናት በመጀመሪያው ዙር ከጥር 10 እስከ የካቲት 05/2010ዓ.ም፣ በሁለተኛው ዙር ከግንቦት 25 እስከ ሰኔ 05/ 2010ዓ.ም፣ በሦስተኛው ዙር ከነሐሴ 11 እስከ መስከረም 25/2011ዓ.ም፣ በአራተኛው ዙር ከመስከረም 01 እስከ 27/2012 ዓ.ም፣ በአምስተኛው ዙር ከጥር 12 እስከ 19/2012ዓ.ም ድረስ እንዲሁም ለተጨማሪ የቡድን ውይይት ከመጋቢት 15 እስከ 20/ 2013ዓ.ም በመሐል በመሐልም ልዩ ልዩ ከበራዎች በሚኖሩበት ወቅት በመገኘት በምልከታ ያገኘናቸውን መረጃዎች በመቅረፀ ድምፅ፣ በቪዲዮ እና በፎቶግራፍ ካሜራ በመታገዝ ሰብስበናል፡፡ የሰበሰብነውንም መረጃ ተጠቅመናል፡፡

ቦኩ፣ ለአባ ሙዳ፣ እንዲሁም ለባህሉ ቅርበት ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች[15] ተመሳሳይ ጥያቄዎችን አቅርበን አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ችለናል፡፡

#### 2.2.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት

በቃለ ምልልስ እና በምልከታ ከተገኙ መረጃዎች መካከል አጥጋቢ ምላሽ ያልተገኘባቸውን ጉዳዮች በመለየት የተተኳሪ ቡድን ውይይት አድርገናል፡፡ ለዚህ መጣጥፍ ዝግጅት ለተተኳሪ ቡድን ውይይት 9 የሴት መረጃ አቀባዮችን አንድ ቡድን፣ በተመሳሳይ 9 የወንድ መረጃ አቀባዮችን ሁለተኛ ቡድን በ14/01/2012 ዓ.ም በጂሌ፣ 9 አባላት ያሉትን ወንድ እና ሴት መረጃ አቀባዮችን በመቀላቀል ደግሞ በ16/07/2013 ዓ.ም በጨፌ ቱማ ሦስተኛውን የቡድን ውይይት በማድረግ የተጣራ መረጃ በመሰብሰብ ለትንታኔ ተጠቅመናል፡፡ በዚህም ዘዴ ህብረተሰቡ ከከበሩ ንዋያቱ ጋር ያለውን ትስስር፣ ከአጠቃቀም አንፃር መደረግ ስላለባቸው እና ስለሌለባቸው ጉዳዮች ተወያይተን ከትንታኔው አካል አካተናል፡፡

## 3. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ርዕስ ውስጥ ሁለት ጉዳዮች ተቃኝተዋል፡፡ አንደኛው የፅንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች ዳሰሳ፣ ሁለተኛው ደግሞ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ነው፡፡

### 3.1. ጽንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፍ

በንዑስ ርዕሱ ውስጥ የትዕምርት እና ምልክት ፅንሰ ሃሳብ ምንነት ከጥናቱ መመልከቻነት አንፃር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### 3.1.1. ምልክቶች

ምልክቶች (Signs) በማኅበረሰቡ ዘንድ ትርጉም ያላቸው እና አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሃሳቦችን በመወከል ኅብረተሰቡን እርስ በርስ የሚያግባቡ ናቸው፡፡ ዓይነታቸውም ፍቺያቸውም እንደየማኅበረሰቡ ተጨባጭ ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል (Danesi, 2004: 3፤ ሰለሞን፣ 2007 ዓ.ም፣ 290)፡፡ ምልክቶቹም እንደየሀገሩ እና ህብረተሰቡ ማህበራዊ እና ስነልቦናዊ አተያይ ልዩ ልዩ ፍቺዎችን ሊይዙ ይችላሉ፡፡ እንደ ጸሐፊዎቹ ገለፃ ልዩ ልዩ ደንቦችን እና የትራፊክ ሙብራት ምልክቶችን፣ ምስጢራዊ ጽሑፎችን እና ማስታወሻዎችን ወዘተ. የሚያመለክቱ ሲሆን በቅርፅ፣ በመጠን፣ በዓይነት ብዙ ናቸው፡፡ የምልክት ፍቺ ይበልጡን የኅብረተሰቡን ባህል መሠረት የሚያደርግ ሲሆን ከምልክት ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ የሆነው ትዕምርት እንደሚከተለው ተዳሷል፡፡

[15] ለዚህ መጣጥፍ በጥቅሉ 100 ሰዎች (70 ወንድ+30 ሴት) ከነዚህም የከበሩ ንዋያቱን አሰራርና ፍቺ በተሻለ ሁኔታ የሚያውቁ በጥቆማ መልክ 72 (63 ወንድ+9 ሴት) በቁልፍ መረጃ አቀባይነት 28 (23 ወንድ+ 5 ሴት) ተሳትፈዋል፡፡

### 3.1.2. ትዕምርት

ትዕምርት (Symbol) አንድን ነገር ወይም ቁስ የሚወክል ሲሆን ለፎክሎር ጥናት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ፅንሰ ሃሳብ ነው (ሰለሞን፣ 2007 ዓ.ም)፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ከምልክት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው ሲሆን ሁለቱም ትኩረታቸው ቁሳዊ ባህል (Material culture) ላይ ነው፡፡ ትዕምርቶች (Symbols) የማህበራዊ ቁስ ምድብ ናቸው፡፡ ጥቅማቸው፣ ብያኔያቸውም እና ውክልናቸው የሚወሰነው ኅብረተሰቡ በተስማማበት መልኩ ነው (Charon 1989: 39)፡፡

ትዕምርት የቁሱን ውክልና የሚያጎላ፣ ምልክታዊ ትርጓሜ ወይም ሐቲት (discourse) የሚሰጥበት ነው፡፡ ቁሶች፣ ምልክቶች እና ልዩ ልዩ ትዕምርቶች የሚተነተኑበት ሲሆን፣ ትዕምርት የማህበረሰቡን ባህል እና ወግ፣ ፍልስፍና እና የዓለም አተያይ፣ እውቀት እና ጥበብ፣ እምነት እና ኃይማኖት የመሳሰሉትን መነሻ በማድረግ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሃሳብን ይይዛሉ፡፡ ቃላት፣ ቅርጻቅርጽ እና ቁሳዊ ባህል፣ ድምፅ፣ ስዕል፣ ምልክት የመሳሰሉትም እንደ ትዕምርት ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡ በዚህም ሳቢያ ትዕምርት የሁለት ነገሮች ጥምረት ነው፡፡ አንደኛው በዓይን የሚታይ እና ተጨባጭ ምልክት (Sensory sign) ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከሚታየው ነገር ጋር የተያያዘው ሃሳብ ነው (Danesi 2004: 31-32; ሰለሞን 2007፡ 289)፡፡

"ሃሳብ" ሲባል ትዕምርቱ የሚይዘውን ፍቺ ወይም ትርጓሜ የሚያመለክት ነው፡፡ ትዕምርት እንደ ህብረተሰቡ የዕደ ጥበብ አሰራር እና ክሂሎት የተለያየ መልክ እና ዓይነት፣ ቅርጽ እና መጠን አሉት፡ ፡ የማይታዩ የተባሉት አንድ ትዕምርት የሚወክለውን ሃሳብ፣ የሚታዩ የሚባሉት ደግሞ በእጅ የሚዳሰሰውን ቁስ የተመለከቱ ናቸው፡፡ በሁለቱም ዓይነት የሚገኙት ትዕምርቶች የሃሳብ፣ የአመለካከት እና የፍልስፍና መግለጫ ሲሆኑ በውስጣቸውም ልዩ ልዩ ትርጉሞችን አምቀው ይይዛሉ፡፡ ጥናቱም በዚሁ አግባብ ትዕምርቶቹን ፈክሯል፡፡

### 3.1.3. ሥርዓተ ፆታ (Gender)

"የሴትነትን እና የወንድነትን ማህበራዊ ሚና፣ ተግባራትን፣ ስለሴት እና ወንድ ያለውን አስተሳሰብ፣ አመለካከት የሚገልፅ ቃል ነው፡፡ አንድ የተወሰነ ማኅበረሰብ ለወንዶች ወይም ለሴቶች የሰጠው ባህርይ፣ ተግባራት እና ሚና ሥርዓተ ፆታ እንለዋለን" (ሕይወት ኢትዮጵያ፣ 2008ዓ.ም፡ 1)፡፡ ይህም ጥናት ከእንስትነት ጋር የተያያዙ ትዕምርቶች በቱለማ ገዳ ሥርዓት ውስጥ ምን ዓይነት ድርሻ እንዳላቸው ፈትሿል።

### 3.1.4. ሀገር በቀል ዕውቀት

ሀገር በቀል ዕውቀት (Indigenous knowledge) በብዙ ዘመናት ውስጥ የተከማቸ እና የዳበረ፣ ካለፈው ትውልድ የተወረሰ ነባር እውቀት ነው፡፡ ለህብረተሰቡ የተሳካ እና የተረጋጋ ህይወት የሚጠቅም መረጃ፣ ልምድ እና ክሂሎት፣ ሥርዓት፣ እምነት እና ስነመለኮት፣ ቃላዊ ጥበብ፣ የዓለም አፈጣጠር፣ የቀን አቆጣጠር፣ ፍልስፍና፣ ማህበራዊ ተግባቦት፣ ማምረት እና ምርት መሰብሰብ፣ ሽምግልና እና የግጭት አፈታት፣ ባህላዊ ህክምና፣ የአካባቢ ጥበቃ እና የስነምህዳር፣ የዕደ ጥበብ ውጤቶች እንዲሁም እነዚህ ውጤቶች የሚሰሩበትን ባህላዊ እውቀት (ቴክኒክ ወይም ባህላዊ

ቴክኖሎጂ) ያካትታል፡፡ ይህም ሀገር በቀል እውቀት በቃል፣ በሥርዓተ ከበራ እና በተግባራዊ ልምምድ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ነው (The World Bank 1998; Bruchac 2014; UNEP 2008)፡፡ የኛም ጥናት ለሀገር በቀል እውቀት ትኩረት ሰጥቷል፡፡

### 3.2. ንድፈ ሃሳባዊ ዳሰሳ

በንድፈ ሃሳባዊ ዳሰሳ ከአገልግሎት አንፃር ከከበሩ ንዋያቱ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው የሥርዓተ ከበራ ንድፈ ሃሳብ ለጥናቱ መመልከቻነት በጥቅም ላይ ውሏል፡፡

#### 3.2.1. የሥርዓተ ከበራ ንድፈ ሃሳብ (Rituals theory):-

ሥርዓተ ከበራ አንድን ማህበራዊ ኢጋጣሚን ምክንያት በማድረግ የሚከወን ቅደም ተከተል ያለው፤ በቁስና በትዕምርት ታግዞ ትርጉም ባለው እና መልዕክት በሚያስተላልፍ መልኩ የሚፈፀም ድርጊት ነው (Bruce and Yearley, 2006: 263)፡፡ ቀጣዩ ሃሳብም ተደጋጋፊ ነው፣ "ሥርዓተ ከበራዎች ክዋኔያዊ ናቸው፤ በድርጊት የሚፈፀሙ ናቸው፤ ክዋኔዎች ሥርዓተ ከበራዊ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጓዳኝ የራሳቸው መለያ/ኮድ፣ ተደጋጋሚነትም አላቸው - Rituals are performative: they are acts done; and performances are ritualized: they are codified, repeatable actions" (Schenchner, 2015፡ 22). የከበሩ ንዋያቱን ትዕምርታዊ ፍቺ ለማጥናት ሥርዓተ ከበራ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ስላለው ትንታኔውም በዚሁ ረገድ ተተንትኗል፡፡

### 3.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በጽንሰ ሃሳብ እና በንድፈ ሃሳብ ማዕቀፎች ውስጥ ከተጠቀሱት የምርምር መመልከቻዎች በተለይም ከምልክት፣ ትዕምርት፣ ተምሳሌታዊነት ሥርዓተ ፆታ ዕይታ አንፃር የተጠና ጥናት አላገኘንም፡፡ የነዚህንም የከበሩ ንዋያት ትዕምርታዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ትውፊታዊ እሴቶቻቸውን፣ ከበራዊ ሚናቸውን በዝርዝር የሚያሳዩ ጥናቶችም አልገጠሙንም፡፡ ነገር ግን ከፎክሎር ዘርፍ አኳያ ከእንስትነት ጋር የሚያያዙ ጉዳዮችን የሚያነሱ ጥናቶች እንዳሉ ተረድተናል፡፡ ከነዚህም መካከል፡- Kuwee Kumsa (1997)፣ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ የሚታየውን የሲንቄን ተቋማዊ ገፅታ በመጣጥፍ መልክ አቅርባለች እንዲሁም የኔዓለም አረዶ (2000ዓ.ም) በኮኮሳና ገደብ ሀሳሳ ወረዳዎች የሚስተዋለውን የአርሲ ሴቶችን አልባሳት እና ጌጣጌጥ በማጥናት፤ Jemila Adem (2014) በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት፣ በአርሲ በተለይም በአዳሚ ቱሉ ኮምቦልቻ ወረዳ በሚኖሩት ኦሮሞዎች ዘንድ ሲንቄ በሀገር በቀል የግጭት አፈታት ረገድ ያላትን ሚና በመተንተን ለማስተርስ ዲግሪ ከፊሉን ለማሟላት የቀረቧቸው ጥናቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡[16]

በሦስተኛ ዲግሪ ደረጃ ከተሰሩ ጥናቶች መካከል ለኛ ጥናት በተዘዋዋሪ መንገድ ቅርበት ያላቸው፡- ቀነዓ ለሚ (2010ዓ.ም)፣ "የኦሮሞ ሚቶሎጂ ይዘታዊ ትንተና"፤ የጥላሁን ተሊላ (2007 ዓ.ም)፣ "የቱለማ ኦሮሞ መርሣ ወቅቶች ፎክሎር አውዳዊ ጥናት" በሚል ርዕስ ለፒ. ኤች. ዲ ማሟያ የቀረቡት ጥናቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ሁለቱም ጥናቶች በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ይልቁንም

[16] የተዘረዘሩት ለዚህ ጥናት የቀረቡ ናቸው ለማለት እንጂ ሌሎች በርዕስ ያልተጠቀሱ ጥናቶችም ሊኖሩ እንደሚችሉ ልብ ይሏል፡፡

የጥናቱን ቦታ በመጋራት ከኛ ጥናት መጠነኛ ቅርበት ያላቸው ሲሆን የመጀመሪያው የቀነዓ ለሚ ጥናት ዋና ዓላማ፣ “በኦሮሞ ሚቶሎጂ ይዘት ላይ ማህበራዊ ትንተና በማድረግ በኦሮሞ ኅብረተሰብ ባህል ውስጥ ሚቶሎጂ የሚወጣቸውን ተግባራት ማመልከት ነው” (2010ዓ.ም፡ 22)፡፡ በዚሁ መሠረት የመግለፅ ተግባር ያላቸውን የአፈጣጠር እና የአመሰራረት ሚቶችን፣ በዕለታት እና ስነከዋክብት ጥምረት ላይ የተመሰረቱ ሚቶችን፣ የእሬቻ፣ የቦኩ እና የከበራ ሚቶቸን በጥናቱ ተንትኗል፡፡

የኛ ትኩረት ደግሞ የከበሩ ንዋያት ትዕምርታዊ ፍቺ ነው፡፡ በኛ ጥናት የተተነተኑት ጫጩ፣ ጨሌ፣ ሲንቄ፣ ጋዲ፣ ኦኮሌ፣ ጪጮ፣ ጋዮ እና ጡንጦ በቀነዓ ጥናት ውስጥ በቃላት መፍቻ ደረጃ እንጂ በትንታኔ አልቀረቡም፡፡ በተመሳሳይ የጥላሁን ተሊላ ጥናት በቱለማ ኦሮሞ ወቅቶች ፎክሎር አውዳዊ ጥናት ዓብይ ጉዳይ ከሆነው “መርሣ/ liminality” ጋር በተያያዘ ወቅቶች ከቱለማ ኦሮሞ አንፃር በጥልቀት የሚገልፅ በመሆኑ ከኛ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የለውም፡፡ ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖረውም ግን በቱለማ ኦሮሞ መርሣ ወቅት በፎክሎር ዘውጎች የተገለፁ ትዕምርቶችን፣ የቱለማ ኦሮሞን የትዕምርት አመሰራረት እና በቱለማ ኦሮሞ መርሣ ወቅት የታዩ ጉዳዮችን በመተንተኑ ለኛ ጥናት የተሻለ ቅርበት አለው፡፡

በሌላ በኩል፣ ብሩ (2002ዓ.ም)፤ ታቦር ዋሚ (2006 ዓ.ም)፣ ዓለማየሁ እና ሌሎች (2000ዓ.ም)፤ Dirribii (2016) በአማርኛ እና በአፋን ኦሮሞ ለህትመት ባበቁት የታሪክ እና የባህል መጻሐፍት ውስጥ የተወሰኑ የከበሩ ንዋያትን ስያሜ የቃላት ብያኔ በሚመስል ደረጃ ዘርዝረዋል፡፡ አቀራረባቸው ትዕምርታዊ አይደለም፤ ትዕምርቶቹም በማን፣ ለምን፣ እንዴት እንደሚዘጋጁ እና መቼ አገልግሎት እንደሚሰጡ ከፎክሎር አንፃር አይገልፁም፡፡ ትዕምርታዊ ፍቺያቸውንም ከፎክሎር አንፃር በምልዓት አያሳዩም፡፡ እነዚህ ጥናቶች ምንም እንኳ እንስትነትን የተመለከቱ መረጃዎችን ያቀረቡ ቢሆኑም ከርዕሳቸው መገንዘብ እንደሚቻለው ከኛ ጥናት ጋር በተዘዋዋሪ እንጂ በቀጥታ የሚገናኙ አይደሉም፡ ፡ የቦታ እና የርዕሰ ጉዳይ ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው አንዳንዶቹም ለምሳሌ Kuwee (1997) እና Jemila (2014) ጥናቶች በሲንቄ ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የተሰሩ ናቸው፡፡

ትኩረቱን በቱለማ ገዳ ሥርዓት ውስጥ የሚስተዋሉትን እንስትነትን የሚገልፁ የከበሩ ንዋያት ትዕምርታዊነት በማሳየት ላይ ያደረገው የኛ ጥናት ግን ፎክሎራዊ፣ ጽንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ጉዳዮችንም በማካተት የቀረበ ነው፡፡ በተጠቀሱት ጥናቶች ውስጥ ያልተካተቱ የከበሩ ንዋያትን እንዲሁም ሚናቸውን ስለሚተነትን ይለያል፡፡ ዋናው ጉዳያችን ትዕምርት እና ምልክት ናቸው፡፡ ጥናታችንም ከፎክሎራዊ እና ትዕምርታዊ ዕይታ የተቃኘ በመሆኑ እንዲሁም የከበሩ ንዋያቱን ትንታኔ ከከበራ ጋር አጣምረን ስላቀረብን መለያ ነጥቦቻችን ናቸው፡፡

የከበሩ ንዋያቱ በማን እንደሚሰሩ፣ በማን እና መቼ እንደሚያዙ ከባህላዊ ገፅታዎቻቸው ጋር በምስል አስደግፈን ማቅረባችን በተለይም በመጽሐፍ መልክ ከታተሙት የታቦር (2006 ዓ.ም)፣ የድርቢ (2016)፣ የብሩ ሥራዎች ይለያል፡፡ የኛ ጥናት ከቱለማ ገዳ አንፃር በእንስትነት ትዕምርቶች ላይ በመመስረት ዕድሜ እና ማህበራዊ ደረጃን የሚያሳይ እንዲሁም ሥርዓተ ፆታን ያካተተ ጥናት በመሆኑ የራሱ የሆነ አዲስ አቀራረብ ያለው ነው፡፡ ነገር ግን በኛ ጥናት ውስጥ የተተነተኑትን ጉዳዮች ከማጎልበት አንፃር የተጠቀሱት ጥናቶች ጠቀሜታቸው በእጅጉ የጎላ ነው፡፡ ስለሆነም በማጣቀሻነት ተጠቅመንባቸዋል፡፡

## 4. እንስትነትን የሚገልፁ የቱለማ ኦሮሞ ገዳ ሥርዓት የከበሩ ንዋያት ትዕምርታዊ ትንተና

የጥናቱን ትንታኔ በተመለከተው በዚህ ርዕስ ውስጥ እንስትነትን የሚያመለክቱ የቱለማ ኦሮሞ ገዳ ሥርዓት ትዕምርቶች ተገልፀዋል፡፡ በቅደም ተከተላቸውም መሠረት ቀርበዋል፡፡

### 4.1 ጫጬ - Caaccuu

ጫጬ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ከገዳ ሥርዓት በተለይም ደግሞ ከዋቄፈና እምነት ጋር በተያያዘ ከሚታወቁት የከበሩ ንዋያት መካከል አንዱ ነው፡፡ በባህሉ መሠረት የተከበረ የእንስትነት ምልክት ነው፡፡ አዘገጃጀቱ እና ትርጓሜው የሚከተለውን ይዘት አለው፣ "ጫጬ የኮርማ በሬ ቆዳ ለሁለት ተሰንጥቆ፣ በላዩ ላይ ዛጎል ይሰፋል፡፡ በላዩ ላይ የሚንጠለጠለው ዛጎል እኩል ረድፍ እና ቁጥር አለው፡፡ ጫጬ እና ጨሌ የእንስት የከበሩ ንዋያት ናቸው፡፡ የእንስት መራቢያ አካል ተምሳሌት (ምልክት) ነው" (አቶ ነገሣ ነገዎ፣ 11/12/2010 ዓ.ም አዱላላ - በትርጉም የቀረበ)፡፡

አዘገጃጀቱ እና ትርጓሜው የራሱ ደንብ እና ፍቺያዊ ሀተታ ያለው ቢሆንም ጫጬ ከነዛጎሉ የሴት ልጅ መራቢያ ወካይ ነው፡፡ በመረጃ ሰጪው የተገለፀውን ተምሳሌታዊነት አንዳንድ ጽሑፋዊ መረጃዎችም በተመሳሳይ ያጠናክራሉ፣ (ታቦር 2007ዓ.ም፣ 210)፡፡ ጫጬ የሴት ልጅን ክብር፣ ማህበራዊ ደረጃን እና ተቀባይነትን የሚገልፅ የከበረ ንዋይ ነው፡፡ በተከታይ የቀረበው ሃሳብም ይህንኑ አገላለፅ ይበልጥ የሚያጎለብት ነው፣ "የሴቶች የከበረ ንዋይ ነው፡፡ የዋቄፈና እምነት የሚከወንበት ነው፡፡ ከዚሁ በተጓዳኝ ባህላዊ የውበትና የአምልኮ፣ የልምላሜ እና የትውልድ መቀጠልን የሚገልፅ ነው" (የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ 2000፡ 232)፡፡

ጫጬ የተለያዩ ኃይማኖታዊ ስነስርዓቶችን ለመስፈፀም የሚያግዝ በመሆኑ ይበልጡን ከዋቄፈና[17] እምነት ጋር የተሰናሰለ ነው፡፡ ባህላዊ ስነስርዓቶችን እና እንደ እሬቻ ያሉ ባህላዊ ከበራዎችን በመከወን፣ በገዳ ሥርዓት ውስጥም ዕርቀ ሰላም በማውረድ፣ የጉማ ሥርዓትን በማስፈፀም ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ጫጬ በርካታ አገልግሎት አለው፣

> *የሴትነት ክብር መግለጫው፡፡ ጫጬ ወንዝ ወርዶ ወንዙን ያስታርቃል፤ ዝናብ ካልዘነበ ዋቃ (እግዚአብሔር) ዝናብ እዲሰጥ ያደርጋል፡፡ ሰማይ እና ምድርን ያስታርቃል፡፡ መካን የሆነች ሴት ለምና ልጅ ታገኝበታለች፡፡ ልጅ የሌላት ሴት ደግሞ የጉድፈቻ ልጅ ትወስድበታለች፡፡ የተጣሉ ሰዎችን ያስታርቃል፡፡ ጫጬ ወጥቶ አጥቶ አይገባም (አቶ ደሜ አብቹ፣ 21/01/2012 ዓ.ም አዳማ - በትርጉም ቀረበ)፡፡*

"ጫጬ ወጥቶ አጥቶ አይገባም/Caaccuun ba'ee dhabee hingalu" ሲባል፣ የወጣለትን ዓለማ አሳክቶ ይመለሳል እንጂ ሳይሳካለት አጥቶ አይመለስም፣ ጫጬን ይዞ የለመነ (የጠየቀ) አያጣም

[17] ዋቄፈና በአንድ አምላክ የማመን አስተምህሮ ላይ የተመሠረተ የኦሮሞ ብሔር ነባር ኃይማኖት ነው፡፡ ይህም አይነቱ በአንድ አምላክ የማመን እምነት ጥንታዊና ለሌሎችም ኃይማኖቶች መነሻ እንደሆነ ይነገራል (ዓለማየሁ፣ 1998፡ 32፤ ሰለሞን 2010ዓ.ም፣ 41)፡፡

የሚል ሃሳብ የያዘ ነው፡፡ በዚህም ክብሩ ከዋቄፈና እምነት ከለቻ ጋር በተጓዳኝ ይታያል፡፡ ጫጬ ወንዝ ወርዶ ወንዝን ያስታርቃል ማለት ቢጋው ከበረታ፣ ዝናብ ከጠፋ ለዋቃ በሚደረግ ምልጃ እና ፀሎት ዝናብ ያስገኛል ለማለት ተፈልጎ ነው፡፡ ለዚህም ምስክርነት የሚሰጡ አሉ፣ "ሲንቄ፣ አኮሌ፣ ጋዲ፣ ጫጬ ይዘን ወንዝ እንወርዳለን፡፡ ዋቃን እንለመንበታለን፡፡ ከሲንቄ ጋር ጫጬንም የገዳ ሥርዓትን፣ የፀሎት ስነስርዓትን እንከውንበታለን፤ ዝናብ ካልዘነበም እግዝአብሔርን ተማፅነን ያዘንብልናል" (ወይዘሮ ሎኒ መርጋ፣ 27/06/2011 A.L.I. ጎራ ለማን)፡፡

ከላይ የቀረበው ገለፃ ጭምቅ ሃሳብ እንደሚያሳየው፡- ጫጬ ዋቃን ማመስገኛ እና መማፀኛ ነው፤ የሴትነት ክብር ነው፤ የከበራ መተግበሪያ ነው፡፡ የቅድስና እና የንፅህና ትዕምርት በመሆኑም በርካታ አገልግሎትም ፍቺም አለው፡፡ በዋቄፈና አስተምህሮ መሠረት ይህም ሁኔታ ዋቃን (አምላክን/ እግዚአብሔርን) በንፅህና ከማገልገል እና ከማመስገን እና ከመማፀን ጋር የተዛመደ ስለሆነም በባህሉ መሠረት ጫጬን የምትሸከም አንዲት ሴት በመልካም ስነምግባሯ የታወቀች እና በዚህ ባህሪዋ የተከበረች፣ የተጣሉ ሰዎችን የምታስታርቅ፣ ለራሷም በሰዎች ላይ ቂም የማትይዝ (ቂመኛ ያልሆነች) መሆን አለባት፡፡ የማታዳላ፣ ለሁሉም ሰው እኩል የሆነች ናት፡፡

የዛጎሎቹ ረድፍ እና ቁጥር እኩል መሆንም ይህንኑ እኩልነትን፣ ሥርዓተ ፆታን፣ ትውልድ እና ሀብት ማፍራትን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ጫጬ ለእንስነቷ፡- የክብሯ፣ የእሷነቷ እና የፍትሐዊነቷ መገለጫም ምልክቷም ነው፡፡ ጫጬ የመንፈሳዊነት ፀጋ፣ የኅብረተሰቡን ባህል እና ትውፊት፣ እምነት እና አስተሳሰብ በቅጡ በሚያውቅ ባለሙያ፣ በዚሁ የዕደ ጥበብ ዘርፍ በሚገኝ የረዥም ጊዜ ልምድ እና ማህበራዊ አስተውሎት ባላት ሴት/ባለው ወንድ ወይም በአያንቱዎች የሚበለፅግ[18] (የሚሰናዳ) ነው፡፡ በዚህ መልኩ በጥንቃቄ የበለፀገው ጫጬ ከቤተሰብ ወደ በኩር ልጅ፣ በኩር ልጅ ከሌለ ወደ ተከታዩ ልጅ ሚስት በኩል እየተላለፈ እና እየተወራረሰ የሚሄድ ነው፡፡ ቀጥሎ የሚታየው ጫጬ በአያንቱ[19] አበበ የተሰራ ነው፣

---

[18] የከበረ ንዋይ በለፀገ (Ulfaan magarfame) እንጂ ተሰራ አይባልም፡፡ ተሰራ የሚለው ቃል ይበልጡን በማንኛውም ሰው፣ በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ ለሚሰራው ቁሳቁስ ወይም ዕቃ (Meeshaa, mi'a) የሚያገለግል ሲሆን የከበረ ንዋይ (Ulfaa) የራሱን አገላለፅ እንዳለው መረዳት ያስፈልጋል፡፡

[19] "አያንቱ"፣ "ቃሉ" እና "አባ ሙዳ" የተሰኙት ስያሜዎች በአቻነት የሚያገለግል ሲሆን፣ ትርጓሜውም የዋቄፈናን እምነት አስተምህሮ የሚያውቅ እና እምነቱን የሚመራ አባት ማለት ነው፡፡ በኦሮሞ እምነት መሠረት ድሮ ቃሉ ከሰማይ የወረደ ቅዱስ ነው ተብሎ ይታመናል (አቶ ማሞ ገዳ፣ 08/12/2011 ዓ.ም አዳማ)፡፡



*ፎቶ 1. በኢያንቱ (ቃሉ) አበበ ታዬ የተሰራው ጫጬ የፊት እና የኋላ ገፅታ ቦሰት 05/02/2012 ዓ.ም*

በዚህ ጫጩ አናት ላይ የምትታየው ፀሐይ ናት፡፡ ፀሐይ ለዓለም ብርሃን የምትለግስ ናት፡፡ ከፀሐይዋ በታች በእጁ ወዴቻ የያዘ የአባ ገዳ ምስል በወካይነት ይታያል፡፡ ኦዳ ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ትዕምርት ነው፤ ቅዱስ ዛፍ ነው፡፡ የኦሮሞ ህዝብ በገዳ ሥርዓት እና በአባ ገዳ የሚተዳደር መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከፊትና ከጀርባ ያለው ጫጩ ርዝመት እና ስፋት፣ የተጌጠበት ዛጎል እኩል ነው፡፡ ተመጣጣኝ ነው፡፡ ከፊት አባ ገዳ እንዳለው ሁሉ፣ በእኩልነት ከጀርባ ሀደ' ሰንቄ (Haadha siinqee) አለች፡፡

ሀደ' ሲንቄ የአባ ገዳው ሚስት ናት፡፡ አባ ገዳው የገዳ አባት፣ የገዳው መሪ እንደሆነ እርሷም የገዳ እናት "እመ ገዳ" ናት ማለት ነው፡፡ የቅርፅ እና የቁጥር መጠኑ እኩል የመሆን ሚስጠርም እንደተገለፀው ይህንኑ ሥርዓተ ፆታዊ አተያይ እውን የሚያደርግ ነው፡፡ በንዑስ ርዕሱ ከተጠቀሰው የጫጩ ክብር በተጨማሪ በፎቶግራፍ ተደግፎ በቀረበው መሠረት የቱለማ ኦሮሞ ህዝብ የጥበብ እና የፈጠራ ውጤት ማሳያ ጭምር ነው፡፡ አሰራሩ እና ቅርፃዊ መዋቅሩ ከቦታ ቦታ፣ ከሰው ሰው መጠነኛ ልዩነት ቢኖረውም፣ በጭብጣዊ ይዘቱ የህብረተሰቡን ባህል እና ትውፊት፣ እምነትና ፍልስፍና የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

ጫጩ በወንዝ እና በተራራ ላይ ለሚደረግ የምስጋና እና የምልጃ ፀሎት፣ ለተለያዩ እምነታዊ ተግባራት እና ለዕርቅ ሰላም፣ ለሥርዓተ ከበራ ካለው አገልግሎት ባሻገር በቤት ውስጥም እንደ አቴቴ ለመሳሰሉ ኃይማኖታዊ ክዋኔዎች መከወኛነት ይጠቅማል፡፡ በባህሉ መሠረትም አንዲት መሃን

ሴት ልጅ እንድታገኝ በጫጩ ይፀለይላታል፤ ዋቃ ማህፀኗን እንዲያለመልመው ይለመንላታል፡፡ ይህም የመውለድ ጉዳይ ካልተሳካላት ጫጩ ተሸክማ ልጅ ካላት ሴት የጉዲፈቻ ልጅ ትለምናለች፡፡ በባህሉ መሠረትም ይሰጣታል፡፡ በዚህም ምክንያት በልጅ ማጣት የተነሳ በባል እና ሚስት መካከል በሚፈጠር አለመግባባት ሳቢያ ትዳሯ እንዳይፈርስ፣ ማህበራዊ ህይወቷም እንዳይናጋ ጫጩ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ስለሆነም ጫጩ ለእንስቷ መለያ ትዕምርትም፣ ክብሯም ጌጧም ነው፡፡ የማህበራዊ ደህንነት ዋስትናዋም ጭምር ነው፡፡ የህዝቡን ትውፊት እና እምነትም የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በጥናቱ ትንታኔ እንደተገለፀውም በጉዲፈቻ፣ በጉማ ሥርዓት እና በዕርቅ ስነስርዓት ወቅት ጫጩ እና ከለቻ ብዙውን ጊዜ ሳይነጣጠሉ በአቻነት[20] ሲቀርቡ በመስክ በነበረን ቆይታ ተመልክተናል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ አፅንዖት የሚሰጠው ጉዳይ ጫጩ ከነዛጉሉ የእንስትነት (የሴትነት) ትዕምርት ነው፡፡ አሁን አሁን ወንዶችም በአልባሳት ላይ ዛጎልን በፋሽን መልክ በጌጥነት ሲጠቀሙ ይስተዋላል፡፡ ባህሉን የሚያውቁ አዛውንቶች ግን ትክክል እንዳልሆነ ይናገራሉ፣ "ወንድ ዛጎል አያደርግም፡፡ ዛጎል የሴት ነው፡፡ ጨሌም የሴት ነው፡፡ ይህ ትክክል አይደለም፤ ባህላችን አይደለም" (አቶ ነገዣ ነገዎ 23/11/2014 ዓ.ም ቢሾፍቱ)፡፡ በተሰመሳሳይ ጨጮ እና ሲንቄን መያዝ የማይገባቸው ያልተዳሩ ትናንሽ ታዳጊ ህፃናት እና ወጣቶች ሲጠቀሙ ይስተዋላል፡፡ ይህ ዓይነቱ አጠቃቀም ትክክለኛውን ትርጓሜ ያዛንፋል፡፡ በዚህ ረገድ ሊወሰድ የሚገባው መፍትሔ በይሁንታ መልክ ቀርቧል፡፡ ቀጣዩ ርዕስ ጨሌን የተመለከተ ነው።

### 4.2. ጨሌ - Callee

ጨሌ የተለያየ መጠን እና ቀለማት ያለው፣ ከተለያዩ ማዕድናት ወይም የከበረ ድንጋይ (ክቡር ድንጋይ) የሚሰራ ሲሆን በክር፣ በሲር (ጅማት)፣ በቀጭን ቆዳ፣ ሽቦ ወዘተ. ላይ ተጠልፎ በግንባር፣ በፀጉር፣ በጆሮ፣ በአንገት፣ በደረት፣ በእጅ ላይ የሚደረግ ወይም የሚጠለቅ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993፡ 564)፣ "ጥቃቅን እና ክብ ሆኖ ከመስታወት ማዕድን በተለያዩ ቀለማት የተሰራ፣ በክር ተሰክቶ የሚያያዝበት ቀዳዳ ያለውና ለአምልኮት፣ ለጌጥ የሚጠቀሙበት ዶቃ መሰል ጌጥ" በማለት ተቀራራቢ ብያኔ ሰጥቷል፡፡

በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ በሚሰጠው ፍቺ መሠረት የእንስትነት፣ የወላድነት፣ የሙብዛት እና የትውልድ ሐረግ ቀጣይነት ትዕምርት ነው፡፡ በቀረበው ሐተታ መሠረት በገዳ ሥርዓትና በዋቄፈና እምነት መሠረት ለህፃናት፣ ላላገቡ ወጣት ሴቶች እና ላገቡ ሴቶች ጌጥም፤ የከበረ ንዋይም፣ ክብርም ነው፣ "ጨሌ ባህላዊ ጌጥ ነው፤ የታፈረ ነው፤ በፀጋ የሚቀበሉት የከበረ ንዋይ ነው፤ የተከበረም ነው፡፡ ስለዚህ ጨሌ ያደረገች አንዲት ሴት ክብረት ናት፡፡ ጨሌ አድርጋ የምትጓዝ ሴት የታፈረች ናት፡፡ የተቀሩት የከበሩ ንዋያት የተከበሩ እደሆኑ ሁሉ ጨሌም የታፈረ (የተከበረ) ነው ማለት ነው" (አቶ ደሜ አብቹ፣ 21/01/2012 ዓ.ም አዳማ - በትርጉም የቀረበ)።

ዛጎል እና ጨሌ በኦሮሞ ሴቶች ዘንድ የእንስትነት መገለጫ ናቸው፡፡ ቀጥሎ የሰፈረው ሃሳብም የቀረበውን የጨሌ ምንነት ገለፃ ይበልጥ የሚያጠናክር ነው፣ "ጨሌ እንደ ጫጩ ሁሉ የውበት እና የመራባት ትዕምርት (ምልክት) ነው፡፡ ሴቶች ዋቃን ልጅ እና የቀንድ ከብት ስጠኝ ብለው የልመና

[20] የጫጩ እና የከለቻን አቻዊ አገልግሎት በተመለከተ የእንስትነት ትዕምርቶቹ ከሥርዓተ ፆታ ዕይታ አንፃር በተሰኘው ርዕስ ውስጥ ተጨማሪ ሃሳብ ቀርቧል፡፡

እና የምኞታቸውን ተስፋ ህብረ ቀለማት ያላቸውን ጨሌ አሰባጥረው በመደባለቅ አስውበው በአንገት ያንጠልቁታል፣ በግንባር እና በራስ ላይ ያደርጉታል" (Dirribii 2011: 51)፡፡

ከድርቢ ጽሑፍ መረዳት እንደሚቻለው አገልግሎቱ ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው ጌጥ ነው፤ ሁለተኛው ከዋቄፈና እምነት ጋር በተያያዘ የከበረ ንዋይ - 'ኡልፋ' ነው፡፡ ለጌጥ የሚውለው ጌጥነቱ ለሰው ልጅ ብቻ አይደለም፡፡ የእንስቶች መጠቀሚያ የሆኑትን ልዩ ልዩ የከበሩ ንዋያት እና የቤት ዕቃዎች ለምሳሌ ጪጮ፣ ኦኮሌ ባህላዊ ቁሶችን ለማስጌጥም የሚያገለግል በመሆኑ ጨሌ አገልግሎቱ ፈርጀ ብዙ ነው፡፡ ጨሌ የዕድሜ ደረጃ መግለጫም ነው፡፡ ልጅነትን፣ ልጃገረድነትን (ድንግልናን)፣ ያልተዳረች መሆኗን ያመለክታል፡፡ በጹሑፉ ከተጠቀሱት የትዕምርትነት መገለጫዎች መካከል የልጅነት መለያ ምልክት የሆነው የጨሌ ዓይነት አንዱ ነው፡፡ በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ በተለይም በገጠር አካባቢ ህፃን ለሆነች ሴት ልጅ "ገፍተራ/ Gaftaraa" የተሰኘው የጨሌ ጌጥ ከላይኛው አናቷ መሀል ለመሀል ፀጉር ላይ ይታሰርላታል፤ በአንገቷም ላይ አንድ ነጠላ/ ንጥል ጨሌ ይደረግላታል፣




*ፎቶ 2. ህፃን ጊሹ ነሞ ገፍተራ ጨሌ በአናቷ ላይ ኢድርጋ-በራ ወረዳ ዳሎታ ቀበሌ 14/ 01/ 2012 ዓ.ም፡፡*

በምስሉ የሚታየው የአናት ላይ ገፍተራ እና ባለ አንድ ዙር ነጠላ ጨሌ የህፃንነቷ መገለጫ ነው፤ መታወቂያዋም ነው፡፡ ሁለተኛው የጨሌ ዓይነት ወጣት ልጃገረዶች የሚያጌጡበት "Callee dubaroo/ የልጃገረዶች ጨሌ" በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ የልጃገረድነት/ የድንግልናነት ትዕምርት ነው፡፡ አንዲት ኮረዳ ይህን ጨሌ አድርጋ ስትታይ እንዳላገባች (እንዳልተዳረች)፤ ድንግል እንደሆነች ይታሰባል፡፡ ይኸውም የልጃገረዶች መለያ የሆነው ጨሌ እንደሚከተለው በፎቶግራፍ ቀርቧል፣



*ፎቶ 3. በሦስት ነጠላ እና አዝራር (የልብስ ቁልፍ) የተሰራ የልጃገረዶች ጨሌ 2013ዓም - ገፈርሰ ኮርማ*

የልጃገረዶች ጨሌ ለልጃገረዷ አንገት እንዲበቃ ተደርጎ በልኳ በሦስት ንጥል፣ የተለያዩ ቀለማት ባላቸው ጨሌዎች የሚሰራ የድንግልናዋ ምልክት ነው፡፡ ጨሌው እንዳይረግፍም ከጫፍ እና ጫፍ እንዲሁም ከመሃል ደጋፊ የሆነ አዝራር ይበጅላታል (ራግዱ ፎሌ፣ 2013ዓ.ም - ገፈርሰ ኮርማ)፡፡ የልጃገረዶች ጨሌ በአሁኑ ወቅት በከተማም ሆነ በገጠር በተለያየ ቅርፅ እና ዲዛይን ይሰራል፡፡ ከነዚህም መካከል በግንባር እና በአንገት ላይ የሚታሰረውን ባለ ዘርፍ (መነሳንስ) ጨሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ ጨሌ በይበልጥ የገዳ ሥርዓት ሰንደቅ ዓላማ መልክ በሆኑት ሦስቱ ቀለማት ጥቁር፣ ቀይ እና ነጭ እንዲሁም በተለያዩ ህብረ ቀለማት ባላቸው ጨሌዎች ተጊጦ የሚሰራ ነው፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ጨሌ ተከታዩ ፎቶግራፍ አብነት ይሆናል፣



*ፎቶ4. ኩለኒ ገበየሁ - በ2011ዓ.ም በቢሾፍቱ በተከበረ የእንግጫ በዓል ወቅት*

"የልጃገረዶች ጨሌ/ Callee dubaroo" ያላገባች ድንግል ሴት ትዕምርት መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይህን የልጃገረድነት ጨሌ ለመጀመሪያ ጊዜ የምትሰራላት ወላጅ እናቷ ናት፡፡ ኮረዳዋ ዕድሜዋ ደርሶ ስትዳር የልጃገረድነት ትዕምርቷ የሆነውን ይህን ጨሌ ፈታ ሌላ ጨሌ ጨምራ ታስፋፋዋለች፤ ወደ

ታች ታረዝመዋለች፡፡ ይኸውም መዳሯን፣ ወደ ቀጣዩ የህይወት እና የኑሮ ምዕራፍ መሸጋገሯን የሚያመለክት ነው፡፡

ወይዘሮ ራግዱ ፎሌ፣ አሹሬ ቦቤ፣ ማቲሌ ቦንሳ፣ ሎኒ መርጋ እንደሚሉት፣ አንዲት ሴት ተድራ ወደ ባሏ ቤት ስትገባ ለጨሌ መስሪያ የሚሆነውን ግብዓት ገዝታ፣ ባህል እና ወጉን በጠበቀ መልኩ ሰርታ የምትሰጣት የባሏ እናት (አማቷ) ናት፡፡ ይህን ጨሌ አድርጋ ስትታይም ድንግል አይደለችም፤ ተድራለች ተብሎ ይታሰባል፤ ይታወቃልም፡፡ ይህም የጋብቻ እና የአቴቴ ትዕምርት የሆነውን ጨሌ የሚመለከት ሲሆን በሁለት እጥፍ ተጠልቆ በአንገት ወደታች የሚለቀቀው የጨሌ ዓይነት ነው፡፡ እንደተገለፀው በዋቄፈና እምነት መሠረት የአቴቴ[21] ወይም የቦረን እናት ጨሌ (Callee Haadha Booran) በመባልም ይታወቃል፡፡[22]



*ፎቶ 5. ከግራ ወደ ቀኝ የወይዘሮ ማቲሌ ቦንሳ ጨሌ፣ ወይዘሮዋ ጨሌያቸውን አድርገው በራ ጎራ ለማን በተባለ ሥፍራ - 27/06/2011 ዓ.ም*

---

[21] በኦሮሞ የዋቄፋና እምነት መሠረት አቴቴ ለሴቶች ተራዳዒ የሆነች እንስት መለኮት /አምላክ ወይም የእንስት ጠባቂ መልዓክ/ Ayyaana dubartii እንደሆነች ይታመናል፡፡ በቱለማ አንዳንድ አካባቢዎች አቴቴ ማረም (Ateetee Maaram) ወይም አቴቴ ሀደ' ቦረን (Ateetee Haadha Booran) በመባል ትታወቃለች፡፡

[22] የኔዓለም (2000ዓ.ም፡ 50) ከዘረዘረቻቸው የአርሲ ያገቡ ሴቶች የጨሌ አይነቶች መካከል፡- የግንባር ጨሌ -"ጨሌ አዳ (Callee Addaa) እና ጨሌ ጃሪ/ ጨሌ ፋጢሜ (Callee Jaarii Callee Faaximee)" በዚህ ጥናት ከተጠቀሱት ጨሌ አዳ እና ጨሌ አቴቴ ጋር በአገልግሎት ይቀራረባሉ፡፡

የአቴቴ ጨሌ ወይም የቦረን እናት ጨሌ በተለያዩ ስያሜዎች ይታወቃል፡፡ ከነዚህም መካከል የጉዬ ዱላ ጨሌ (Callee Guyyee Duulaa)፣ ጨሌ ኢላንሱ (Callee Illaansuu)፣ ጨሌ ሀራ (Callee Haraa) ጨሌ ሎኒ (Callee Loonii) በመባል የሚታወቁት ተጠቃሽ ናቸው (ራግዱ ፎሌ፣ 2013ዓም - ገፈርሰ ኮርማ፤ አቶ ደሜ አብቹ፣ 21/01/2012 ዓ.ም - አዳማ)፡፡

ከመረጃ አቀባዮቹ በተገኘው ማህበራዊ ፍቺ መሠረት የጉዬ ዱላ ጨሌን የምታደርግ እናት ልጇ ወደ ዘመቻ ወይም አደን በሄደ ጊዜ በአንገቷ አድርጋው፣ የአቴቴ ክዋኔን በመከወን ፈጣሪዋን/ ዋቃን ትለምናለች፡፡ የጉዬ ዱላ አቴቴ - የጦርነት አምላክ ናት ተብሎ ይታመናል፡፡ እንዲህም በመሆኑ ወደ ዘመቻ ወይም አደን የሄደ ልጇ በሰላም እና በድል እንዲመለስላት የምትፀልይበት የጨሌ ዓይነት ነው፡፡ ሁለተኛው የአቴቴ ጨሌ ዓይነት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ጨሌ ኢላንሱ የሚሰኘው ሲሆን አንዲት ነብሰ ጡር ሴት ምጥ ሲይዛት ምጥ እንዳይበዛባትና እንዳይበረታባት፣ ወዲያውኑ በሰላም እንድትገላገል በአቅራቢያዋ ያሉ ሴቶች አድርገውት አቴቴን የሚማፀኑበት ነው፡፡ ሌላኛው የጨሌ ዓይነት ጨሌ ሀራ ነው፡፡ ይህ ጨሌ መስከረም ሲጠባ፣ የክረምት ወራት አልፎ የፀደይ ወራት (Birraa) ሲገባ በመልካ (ሆራ/ሐይቅ) ላይ ለሚከናወን የምስጋና በዓል (የእሬቻ በዓል) የሚደረግ ነው፡፡ ጨሌ ሎኒ በበጋ ወራት የዝናብ ወቅት ሲረዝም፣ ወንዞች ደርቀው የቤት እንስሳት እና ሰው የሚጠጡት ውኃ ጠፍቶ ድርቅ (በጋ) በሚበረታበት ወቅት ተደርጎ ፈጣሪ ዝናበ ምህረቱን እንዲያወርድ፣ ዘንቦም መሬትን እንዲያርስ፣ ሣር አብቅሎም ፍጥረታቱን እንዲመግብ በመልካና በተራራ በሚደረግ ፀሎት የሚላመኑበት ነው፡፡ በዚህም አግባብ ጨሌ ለእንስቷ ከጌጥም ባሻገር የእምነት፣ የቅድስና፣ ከተፈጥሮና መንፈሳዊነት ጋር የተያያዘ የከበረ ንዋይ መሆኑን ያመለክታል፡፡

የሴቶች ክብር እና የዋቄፈና እምነት መግለጫ የሆነው የአቴቴ ጨሌ እንስቷ የተዳረች ወይም ያገባች መሆኗን ያመለክታል፡፡ በንዑስ ርዕሱ የቀረበውን ሃሳብ ለማጠቃለል ያህል የአቴቴ ወይም ያገባች ሴት መለያ የሆነው ጨሌ አንዲት ሴት በተለያዩ የዋቄፈና፣ የፀሎት ስነስርዓት እና የገዳ ከበራዎች እዲሁም ጫጩ ይዛ ሰዎችን ለማስታረቅ ስትሄድ የምትጠቀምበት ነው፡፡ ጨሌው በቀኝ እና በግራ አራት አራት በድምሩ ስምንት ዙር[23] ያለው ነው፡፡ የአቴቴ ጨሌ በበኩር (Angafa/ ታላቅ)[24] ልጅ ሚስት በኩል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ነው፡፡ ከባል ቤተሰብ በውርስ የሚተላለፈው ጨሌ እንደሁኔታው እስከ ዘጠኝ ቤት (ዘጠኝ ትውልድ) ሊደርስ ይችላል፡፡ ይህም ትውፊታዊ አሰራር አንድ ቤተሰብ ብዛቱ ከየት ተነስቶ የት እንደሚደርስ ለማወቅ የሚያስችል ሲሆን፣ ዘጠነኛው ትውልድ ላይ ሲደርስም ቤተሰቡ ወደ ንዑስ ጎሣ ያድጋል፡፡ በዘጠኝ ትውልድ ቅብብሎሽ እየተላለፈ የመጣው ጨሌም አዲስ ለሚመሰረተው ጎሣ የከበረ ንዋይ (Ulfaa gosaa) ይሆናል፡፡ በዚሁ ሳቢያ የእንስትነት ትዕምርት ወይም ምልክት ብቻም ሳይሆን መዝገበ ትውልድ ነው፡፡ የትውልድ መዘከሪያ እና ማስታወሻ ነው፡፡ የአያት፣ ቅድመ አያት (Akaakoo Abaaboo) ቅርስ ይሆናል፡፡

[23] የአቴቴ ጨሌ ባለ ስምንት ዙር፣ የአቴቴ ፈጫሳ ክዋኔ ሰስምንት ጊዜ መሆን ከገዳ ሥርዓት ስምንቱ ዓመት የሥልጣን (የአስተዳደር ዘመን) ጋር የሚያያዝ ስለመሆኑ ይነገራል፡፡

[24] በኦሮሞ ባህል ብኩርና (Hangafummaa) ትልቅ ዋጋ ስላለው የከበሩ ንዋያቱንም የላቀ ክብር ይገልፃል፡፡

## 4.3. ሲንቄ - Siinqee

በቱለማ ገዳ ሥርዓት መሠረት አባ ገዳ (ሆሮሮ ገዳ)፣ አባ ወዴቻ (ኡሌ ወዴቻ) እንደሚይዙት ሁሉ ሀደ’ ሲንቄ (Haadha Siinqee) በበኩሏ ሲንቄ ትይዛለች፡፡

ሲንቄ ቀጭን፣ ረዥም እና ቀጥ ካለች የሰፋ (Haroorecha) ወይም የወይራ (Eejersa) ዛፍ እንጨት ተመርጦ የሚሰራ ያገባች ሴት የከበረች ንዋይ ናት “በእንስቷ ቁመት ልክ ተዘጋጅታ ለሴት ሙሽራ በሠርጓ ዕለት ከጪጩ ጋር የሚሰጣት ሲሆን ያገባች ሴት መለያ እና መታወቂያ ምልክት ናት፣ ያላገባች ሴት ሲንቄን አትይዝም፡፡ እኔ አሁን ልያዝ ብል መያዝ አልችልም፡፡ ህጉ ይከለክለኛል፡፡ የተዳርኩ ዕለት እንጂ ከኔ ላይ አያምርም፡፡ ባህሉንም ማበላሸት ይሆናል” (ወ/ሪት ኩሜ ተሾመ፣ 06/12/ 2010 ዓ.ም ቢሾፍቱ - በትርጉም የቀረበ)፡፡

ሲንቄ የእንስትነት የክብር ትዕምርት፤ ሴቴ ፆታን ትወክላለች፡፡ ለተባለው ዓላማ ከሰፋ ዛፍ ተቆርጦ የሚሰራው አዲስ ሲንቄ ከዛፉ ዓይነት የተነሳ ወደ ቢጫነት የሚያደላ ሲሆን፣ በጐጆ ቤት ጣሪያ ላይ ተደርጐ የምድጃ እሳት ጭስ እንዲያገኘው ይደረጋል፡፡ እየዋለ ሲያድር፣ እየቆየ ሲሄድ ወደ ቅላት እና ጥቁረት ይቀየራል፡፡ በቂቤ ወይም በስብ ተወልውሎም ውበት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡ የቀረበውን ገለፃ የሚወክል ሲንቄ በተከታዩ ፎቶግራፍ ተመልክቷል፣




*ፎቶ6. ጫጬ እና ሲንቄ የያዙ የቱለማ እንስት (ሀደ’ ሲንቄ) ከባለቤታቸው (አባ ወዴቻ) ጋር ከህዝቡ ፊት ሆነው ወደ ሆራ ሀርሰዲ ሲጓዙ የሚያሳይ ቢሾፍቱ-24/01/ 2012 ዓ.ም*

በቱለማ ገዳ ሥርዓት የሰማይ እና ምድር ሕግ[25] ሴት ክብርት ናት፤ ሲንቄ ይዛ የምትጓዝ ሴት ደግሞ ትልቅ ክብር አላት፡፡ ምክንያቱም ሲንቄ በራሷ ክብርት ናት፡፡ የሴቷም የክብር እና የኃይል (የሥልጣን) መግለጫ ናት፡፡ ትዕምርትም ናት፡፡ ከዚህ መሰሉ አገልግሎት አንፃር ሲንቄ እንደ አንድ የኦሮሞ ሴቶች ተቋም የሚቆጠር፣ የሴቶች ኃይል እና ምልክት መሆኗን የተለያዩ አጥኚዎች ገልፀዋል (Jemila, 2014: 47; Kuwee 1997, 118)፡፡

ከቤተሰብ ቤተሰብ፣ ከአካባቢ አካባቢ የሚፈጠር ልዩነት ታሳቢ ቢደረግም ይበልጡን ግን ሲንቄ በልጅቷ እናት ተዘጋጅታ በሠርጓ ዕለት ለሙሽራዋ ይሰጣታል የሚለው ሐሳብ ሰፊ ተቀባይነት ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል (ወ/ሪት ኩሜ ተሾመ፣ 06/12/ 2010 ዓ.ም ቢሾፍቱ)፡፡ ሲንቄ ጠብ፣ ጦርነት (ጥል፣ ግጭት) የማቆም ኃይል ስላላት የእርቅ እና የሰላም ትዕምርት ናት፡፡ ከዚሁ ክብር በመነሳት ምንም እንኳ ቢቸኩሉና ቢጣደፉ ሲንቄ ይዛ የምትጓዝን ሴት በአክብሮት ቆመው ያሳልፏታል እንጂ መንገድ አያቋርጧትም (አቶ ቡላ ሀዩ፣ 11/01/2012 ዓ.ም መቂ)፡፡ እንደ መረጃ አቀባዩ ገለፃ ጉዞዋን (መንገዷን) ካቋረጧት ነውር ነው፤ የኅብረተሰቡንም ደንብ ማፍረስ ነው፡፡ ምናልባትም በተለየ ሁኔታ አቋርጠዋት ለማለፍ የሚቻለው ባለሲንቄዋ ሴት የይለፍ ፍቃድ ከሰጠች ብቻ ነው፡፡ አለበለዚያ ክብረ ነክ ድርጊት በመሆኑ ተጠያቂነትን፣ ቅጣትን ያስከትላል፡፡ ሲንቄ ዕርቅ የምትፈጥረው በሰው እና በሰው መካከል ብቻ አይደለም፡፡ ዝናብ ሲጠፋ ሀደ' ሲንቄዎች ወደ ወንዝ ወርደው ስለሚፀልዩ፣ ፀሎታቸውንም እግዚአብሔር ሰምቶ ዝናብ ያዘንብላቸዋል ተብሎ ስለሚታመን ስንቄ ሰውን ብቻ አይደለም ሰማይና ምድርን በማስታረቅ ረገድ ትልቅ ድርሻ አላት፤ Namaa miti, waaqaa fi lafa araarsuu keessatti siinqeen ga'ee olaanaa qabdi ይባላል፡፡ በዚህም ሳቢያ የገዳ ሥርዓትን ለመከወን፣ የዋቄፈና ስነስርዓትን ለማስፈፀም፣ ዋቃንም በመማፀን ዝናበ ምህረት ለማግኘት ከተጠቀሱት የከበሩ ንዋያት ጋር ሲንቄ የጐላ ሚና አላት፡፡ የቀዳማይ እና ካልዓይ መረጃዎችን በማጣቀስ የተዘረዘሩትን የሲንቄ አገልግሎቶች በአምስት[26] ምድብ መግለፅ ይቻላል፣

1. ጦርነት (ግጭት፣ ጠብ) በተነሣ ጊዜ ሀደ' ሲንቄዎች እልልታ እያሰሙ በጦርነቱ (በግጭቱ፣ በጠቡ) መሀል ገብተው ያስቆማሉ፡፡ ይህን እልልታ ቸል የሚል ካለ በገዳ ሥርዓት ቅጣት ይቀጣል (አቶ ቡላ ሀዩ፣ 11/01/2012 ዓ.ም መቂ)፡፡ ነገር ግን በእናቱ የሚጨክን ወገን ስለሌለ፣ ሥርዓት እና ደንቡም ስለማይፈቅድ ጦርነቱም (ግጭቱ፣ ጠቡ) ወዲያውኑ ይበርዳል፡፡ ስለሆነም ሲንቄ ጦርነት የማስቆም፣ ዕርቀ ሰላም እንዲካሄድ… የማድረግ አቅም አላት ማለት ነው፡፡

2. በባህሉ መሠረት ሲንቄን መያዝ የምትችለው ያገባች ሴት ናት፡፡ ነገር ግን ያልተዳረች ኮረዳም ሲንቄን የምትይዝበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ይኸውም አንድ ወንድ ያማረችውን፣ ቀልቡ የወደዳትን ሴት ማግባት እንደሚችል ሁሉ፣ አንዲት ልጃገረድም የሲንቄን ኃይልና ክብር ተጠቅማ ቀልቧ የፈቀደውን ወንድ መርጣ ማግባት ትችላለች፡፡ ይኸውም ድፍን ቡና፣ ለምለም ሣር (እሬቻ)፣

---

[25] "ዋቃ/ አምላክ ክቡር ነው፤ መሬት ክብርት ናት፤ አባት ክቡር ነው፤ እናት ክብርት ናት፤ ተራራ ክቡር ነው፤ ጅረት ክብርት ናት የተሰኙት ናቸው (አቶ ጣፋ በዳ'ዳ'፣ 03/10/2010ዓ.ም ደ'ከ ኮራ)፡፡

[26] አከፋፈሉ (አቶ ቡላ ሀዩ፣ 11/01/2012 ዓ.ም መቂ) በሰጡት መረጃ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

እምቧይ እና ሲንቄ[27] ይዛ ከልጅየው ቤተሰብ ቤት ትሄዳለች (አቶ ቡላ ሀዬ፣ 11/01/2012 ዓ.ም መቂ)፡ ፡ የመጣችበትን ምክንያት ስትጠየቅም፣ "Seenee hinba'u; taa'ee hin ka'u/ ገብቼ አልወጣም፤ ተቀምጬ አልነሳም" በማለት ፍላጐቷ እና ምርጫዋ የወደደችውን ልጅ ማግባት እንደሆነ ትናገራለች፡፡ "እምቢ ልጃችንን አታገቢም" አትባልም፤ እንዲህ ማለት ነውር ነው፣ "በዚህ ዓይነት የመጣችውን ማባረር በባህሉ ውስጥ ሐራም ተደርጎ ስለሚወሰድ፣ ልጅቷን መቀበልን ባህሉ ስለሚያስገድድ ጋብቻው ይፈፀማል" (ሙልጌታ 1997፡27)፡፡ የሕጋዊ ጋብቻ ትዕምርት የሆነችዋን "የረኮ በግ (Rakoo/ረኮ)" ያርድላታል፡፡ ባልም ይሆናታል፡፡ ይህ የጋብቻ አይነት "Aseennaa/ አሴና" ይሰኛል[28]፤ በአማርኛ ወዶ ገብ ሊባል ይችላል፡፡

3. አንዲት ሴት ተድራ በአምስተኛው ቀን መናገር ያልጀመረ ሕፃን ልጅ ተሸክማ፣ ሲንቄዋን ይዛ፣ ጨሌዋን አድርጋ በቤተሰቡ በረት ውስጥ ከሚገኙት ጊደሮች የፈለጋትን፣ መልኳ ያማራትን መርጣ እንደ ቤተሰቡ (እንደ ልጅየው) ሀብት አንድም፣ ሁለትም፣ ሦስትም፣ አራትም፣ አምስትም ጊደሮች በሲንቄዋ ትነካለች፡፡ ከዛን እለት ጀምሮ ጊደሮቹ የራሷ ሀብት እና ንብረት ይሆናሉ፡፡ በዓመቱ እሷም ጊደሮቿም ይወልዳሉ፡፡ እርሷም በተራዋ ከባሏ ተማክራ ከተወለዱት ጥጆች መሃል በሲንቄዋ ነክታ ለልጇ በስጦታ ትለግሳለች፡፡ ይህም ልገሳ በአፋን ኦሮሞ "አንዱሩ'ራ/ Andhuuraa" ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን፣ የልጅየው/ የልጅቷ የግል ሀብት ነው፡፡ በዘመኑ ቋንቋ ከልጅነት ዕድሜ የሚጀመር የልጆች የባንክ ሒሳብ ቁጠባ ማለት ይሆናል፡፡

4. የበጋው ወራት ከተራዘመና ድርቅ ከተከሰተ ሴቶች ሲንቄያቸውን ይዘው በእልልታ ወንዝ በመውረድ በአባሯ እግራችን ነው የመጣነው፤ በዝናብ መልሰን በማለት ይፀልያሉ፡፡ በዚህ የፀሎት እና የልመና ስነስርዓት ላይ ወንዶች አይሳተፉም፡፡ ፈጣሪያቸውን እንደተማፀኑትም በአቧራ እግራቸው ሄደው በዝናብ ሲመለሱ ይስተዋላል፡፡ ዝናብ ይዘንባል፡፡[29]

5. አንዲት ሴት ያለ ፍላጐቷ ባለቤቷ ቢደፍራት፣ በተለይም ደግሞ በአራስነት ጊዜዋ ወገቧ ሳይጠነክር[30] ያለ ፍቃዷ በመጠጥ ስሜት ወይም በኃይል ቢደፍራት በምታሰማው እልልታ ወይም በምታቀርበው ስሞታ መሠረት የሰፈሩ ሴቶች ከርሷ ጋር "እልልል..." እያሉ ተቃውሟቸውን ያቀርባሉ፡፡ ይህም የእልልታ ድርጊት "የሲንቄ ጩኸት/ Iyya Siiqqee" (Kuwee 1997, 128) የሚባል ሲሆን እንስቶቹ በአካባቢው ወደሚገኘው የገዳ ዳኛ አበሴር (Abba Seer/ Abbaa Seeraa) ሄደው በማስፈረድ ባልየው ኮርማ በሬ እንዲቀጣ ይደረጋል፡፡ ሴቶቹ ኮርማ በሬውን አሳርደው እና ጠብሰው ይበላሉ፤ የታረደውንም ኮርማ ቆዳ በመሰንጠቅ ተከፋፍለው ሲንቄያቸው ላይ በምልክትነት ያስራሉ፡፡ ባልና ሚስትም ታርቀው፣ ተመርቀው፣ሁሉም በደስታ ወደየቤታቸው ይመለሳሉ (አቶ ቡላ ሀዬ፣ 11/01/2012 ዓ.ም መቂ)፡፡ በትንታኔው እንደታየውም ሲንቄ ዘርፈ ብዙ

---

[27] ድፍን ቡና የእንስትነቷ ወግ፣ ለምለም ሣር (ኢሬቻ) የምሥጋና፣ የተማፅኖ እና የዕርቅ፣ እምቧይ የወላድነት እና የመብዛት፣ ሲንቄ የሴቶች ኃይል እና የሥልጣን ትዕምርት እንደሆኑ ይታሰባል፡፡

[28] ሙሉጌታ (1997ዓ.ም.፡ 27) ይህ አይነቱ ጋብቻ ኦሊጦ (Olixoo) እንደሚባል እና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱን ገልጿል፡፡ ይህም ቃል ከአሴና (Aseennaa) ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡

[29] ይህም በተግባር የሚያጋጥም ሲሆን ብዙውን ጊዜ ወዲያውኑ አልያም በበነጋው እንደሚዘንብ ይነገራል፡፡ ካባህል እና ከእምነት (ሀገረሰባዊ እምነት) ጋር የተሰናሰለ ነው፡፡

[30] ወገቧ ሳይጠነክር ግብረ ሥጋ አለመፈፀሚ ከጤናም ጎን ለጎን ትንሽ ሳትሰነባብት ወዲያውኑ እንዳትፀንስ እና ላይ በላይ ልጅ እንዳትወልድ ወይም የዕፎይታ (የዕረፍት) ጊዜ እንድታገኝ ያግዛታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ጠቀሜታ አላት፡፡ በዚህ ጥናት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ሌላው ጉዳይ በከበሩ ንዋያቱ መካከል ጥብቅ ቁርኝት ወይም መስተጋብር ያለ መሆኑ ነው፡፡ አንዱ ከሌላው ጋር ተጣምረው የሚያዙ ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ጫጩ ያላት አንዷት እንስት በከበራ ላይ ስትገኝ ጨሌ እና ሲንቄን ጨምሮ እንደ ከበራው ዓይነት አኮሌ[31]፣ ጋዮ[32]፣ ጋዲ[33]፣ ጡንጦ[34]፣ ቀቤ[35]፣ ጪጮ[36]፣ እሬቻ[37] የመሳሰሉትን በተጓዳኝ ልትይዝ

[31] አኮሌ (Okolee) በስንደዶ እና በሰበዝ የሚሰፋ ሲሆን፣ ማንጠልጠያው በተለፋ ቆዳ - ነት በባህላዊ አስራር የሚዘጋጅ የሴቶች የወግ ዕቃ ነው፡፡ አሰራሩም በዛጎል ያጌጠ ነው፡፡ ለወተት ማለቢያ፣ ለዲ'ባዩ (Dhibaayyuu) የፀሎት እና የማሥጋና ስነስርዓት ወተት ይዞ ለመገኘት ያገለግላል (ወ/ሮ መሣይ ግርማ፣ 02/02/2012 ዓ.ም ኡዴ - ገርቢቻ፤ ወ/ሮ ማቲሴ ቦንሳ፣ 27/06/2011 ዓ.ም ጎራ ለማን)፡፡

[3]2 ጋዮ ልክ እንደ ጡንጦ ከስሩ ቅል፣ ከላይ ደግሞ ከላላ በሚባል የሀረግ ዓይነት በስንዶዶ እና በሰበዝ የሚሰፋ ነው፡፡ የቅርፅና የመጠን ልዩነት ቢኖራቸውም፣ "ቀቤ/ Qabee" ከተሰኘው ባህላዊ የወተት መያዣ ጋር ይመሳሰላሉ፡፡

[3]3 "ጋዲ ላም በምትታለብበት ጊዜ ወዲያና ወዲህ እንዳትል በእግሯ ላይ የሚታሰር ጠፈር ነው" (የኢ.ቋ.ጥ.ም.ማ፣ 1993 ዓ.ም፣518)፡፡ በቱለማ ገዳ ሥርዓት ህግ የተደነገገለት ከአናቱ ቦኩ ያለው ጋዲ (Gaadii Seeraa) የተለየ ወግና ደንብ አለው (ወ/ሮ ማቲሴ ቦንሳ፣ 27/06/2011 ዓ.ም ጎራ ለማን)፡፡

[3]4 ጡንጦ (Xuunxoo) የተሰኘው ባህላዊ ቁስ የሚሰራው ከቅል፣ ከስንደዶ፣ ከሰበዝ እና ከተለፋ ቆዳ ሲሆን፣ ሙያው ባላት ሴት ዛጎል እና ጨሌ ይጌጥበታል፡፡ ወተት ይጠጣበታል፡፡ ልክ እንደ አኮሌ ሁሉ በከበራ ወቅት ሴቶች ከታች ባለው ቅል ወተት፣ በክዳኑ ለጋ ቅቤ (Dhalee) ይይዙበታል፡፡ በተመሰሳይ አጠራር "xuuxxoo/ጡጦ" ይባላል (አቶ ሀዋስ ከተቦ፣ 25 16/2011 ዓ.ም ዓለምጤና)፡፡

[35] ቀቤ (Qabee) የታችኛው አካል ከቅል፣ የላይኛው አካል ክዳን ከስንደዶ እና ከሰበዝ የሚሰራ ሲሆን ክዳን እና የቆዳ ማንጠልጠያ አበጅተውለት ወተትና ሙዳ (ለጋ ቅቤ-ቅብዓ ቅቤ) ይይዙበታል (ወ/ሮ መሣይ ግርማ፣ 02/02/2012 ዓ.ም ኡዴ - ገርቢቻ)

[36] ጪጮ (**Ciicoo**) ጥሩ ቅርፅና ውበት ካለው ቅል፣ ክዳኑ ደግሞ ልክ እንደ ቀቤ በስንደዶ እና ሰበዝ ተሰርቶለት ለወተት፣ ለበዓላት እና ከበራዎች የሚዘጋጅ ምርጥ እና ልዩ ባህላዊ ምግብ (Dhangaa) መያዣነት ያገለግላል፡፡ በሌላ በኩል ጪጮ የታችኛው አካል ከቅል፣ ከስንደዶ እና ሰበዝ እንደሚሰራ ሁሉ ከሸክላም ይሰራል፡፡ "ጪጮ ሀደ' ሲንቄዎች እና የተዳሩ (ያገቡ) ሴቶች የሚይዟት ሲሆን ይልቁንም ደግሞ "Ciicoo gurraatti/ ጥቁሯ ጪጮ" በአገልግሎቷ እና በቅርስነቷ በቱለማ ኦሮሞዎች ዘንድ ትልቅ ክብር ይሰጣታል፡፡ በቱለማ ምርቃትም ትጠቀሳለች፡፡
(ወ/ሪት ኩሜ ተሸመ፣ 06/12/2010 ዓ.ም ቢሾፍቱ፤ ወ/ሮ መሣይ ግርማ፣ 02/02/2012 ዓ.ም ኡዴ - ገርቢቻ)፡፡

[37]. እሬቻ በዚህ አገባቡ ለዋቃ (ለአምላክ) ምስጋና የሚቀርብ ለምለም ሣር ማለት ነው፡፡ አባሪ አራትን ይመለከቷል፡፡ በሁለተኛው ትርጉሙ በዚህ ለምለም ሣር አማካኝነት ለዋቃ (አምላክ) የሚቀርብ ምስጋና፣ ውዳሴ እንዲሁም ገፀበረከት... ሊባል ይችላል፡፡




ፎቶ 7. ሀደ' ሲንቄዎች - ሲንቄ፣ አኮሌ፣ አሬፋ እና ጪጮ ይዘው በአሬፋ በዓል ላይ ቢሾፍቱ- 25/01/2012 ዓ.ም

ትችላለች፡፡ ጠቀሜታቸውም ጎልቶ የሚታየው በከበራ ወቅት ነው። ከእሬቻ ጋር የተያያዘው ተከታዩ ምስል ጥሩ ምሳሌ ነው፣

በዚህ መጣጥፍ በተናጥልም ሆነ በጋራ የተገለፁት የከበሩ ንዋያት፡- ጫጬ፣ ጨሌ፣ ሲንቄ፣ ኦኮሌ፣ ጋዲ፣ ጪጮ፣ ቀቤ፣ ጡንጦ፣ ጋዮ ናቸው፡፡ ቀጣዩ ርዕስ እንዚህ የከበሩ ንዋት ለጥናቱ መመልከቻነት ከዋሉት ፅንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ዕይታ ጋር ያላቸውን ቁርኝት ያብራራል፡፡

## 5. የውጤት ማብራሪያ

ትዕምርት እና ምልክት ግባቸው ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ሃሳቦችን በመግለፅ ኅብረተሰቡን እርስ በርስ ማግባባት ስለመሆኑ በክለሳ ድርሳናት ተገልጿል፡፡ የጥናቱን ትንታኔም ህዝቡ ለከበሩ ንዋያቱ በሚሰጠው ማህበራዊ ፍቺ ላይ በመንተራስ ለማቅረብ ተችሏል፡፡

በዚሁ መሠረት ጫጬ የዋቄፈና እምነት፣ የገዳ ሥርዓት ከበራ እና የጉማ ዕርቅ መተግበሪያ (ማስፈፀሚያ) ነው፡፡ ይህም በገዳ ሥርዓት ህግ ብሎም በማህበረሰቡ ተፈጥሯዊ እና ማህበራዊ ደንብ (Safuu) እውቅና የተሰጠው ሲሆን ጫጬ ከነዛኅሉ የእንስትነት ትዕምርት/ ምልክት ነው፡፡ ጨሌም እንዲሁ የእንስትነት፣ የወላድነት፣ የመራባት፣ የመብዛት እና የትውልድ ሐረግ ቀጣይነት ትዕምርት ነው፡፡ የአቴቴ ጨሌን ያደረገች ሴት በቅርብ ርቀት ስትታይ የተዳረች ወይም ያገባች ሴት መሆኗ ይታወቃል፡፡ እናም የኃብቻ ምልክት ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እንስቷ የአቴቴ ስነስርዓት ክዋኔ - "ፈጫሳ/ Faccaasaa" የከወነች መሆኗን ያመለክታል፤ ስለዚህ የመንፈሳዊነት እና የከበራ ምልክት ነው፡፡ ጨሌ ዱበሮ ደግሞ የልጃገረድነት፣ የድንግልና ትዕምርት ነው፤ ጨሌ ለእንስቷ ጌጥም ነው፤ ውበቷም ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ ከቀረበው ገለፃ ለመረዳት የሚቻለው ስንቄም

በተመሳሳይ የእንስትነት፣ ያገባች ሴት ትዕምርት ናት፡፡ ከቀረበው ትንታኔ አንፃር በተሰጣት ክብርና ኃይል መሠረት ጠብን፣ ግጭትን፣ ጦርነትን የማብረድ እና የማስቆም ሚና አላት፡፡ በዚሁ አግባብ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ሴቶች ያላቸውን ክብር፣ ሥልጣን፣ ኃይል (Power)፣ ተደማጭት፣ ወሳኝነት፣ እውነተኛነት እና ፍትሐዊነት፣ ሰላማዊነት እና የሰላም ግንባታ ድርሻ፣ ሃሳብን በነፃነት ማንሸራሸር እና የፆታ እኩልነት በሲንቄ ትዕምርታዊነት ይገለጣል፡፡ በባህሉ መሠረት ይህ አይነቱ የእንስትነቷ ሚና ከሲንቄ ጋር የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡

የሲንቄ ክብር የሚመነጨው፣ ዓለማዊ እና መንፈሳዊ ትርጉም የሚሰጠው የሲንቄው ዘንግ ያልተጣመመ እና ቀጥ ያለ (ቀጥተኛ) ከመሆኑ የተነሣ ነው፡፡ ቀጥተኝነት ያልተደበቀ እና ያልተሰወረ ደባ (ጥመትን፣ ክፋትን) የሌለው፣ ግልፅነትን፣ እውነትን፣ ሀቀኝነትን፣ ትክክለኛነትን፣ አለማዳላትን፣ ፍትሐዊነትን ይወክላል (ወይዘሪት ኩሜ ተሾመ፣ 26/01/2012 ዓ.ም ቢሾፍቱ፤ አቶ ሸገና ኮርቤ፣ 10/12/2011 ዓ.ም አዱላላ)፡፡ እንዲህም መሆኑ የሲንቄን የክብር አምሳልነት፣ የባህሪ ተምሳሌትነትን ያጎላል፡፡ በጥናቱ ክለሳ ድርሳን እንደተገለፀው እንዲሁም በፎቶግራፍ ቁጥር 7 እንደታየው ትዕምርቶቹ  እና ምልክቶቹ ህይወት የሚኖራቸው፣ ጠቀሜታቸውም ይበልጡን የሚታወቀው በከበራ ውስጥ ነው፡፡ ይኸውም የሥርዓተ ከበራን ወሳኝነት የሚያሳይ ሲሆን ለዚህም የገዳ ጉዞ (Godaansa Gadaa)፣ የእሬቻ በዓል እና ልዩ ልዩ የክብረ በዓላት ከበራዎች ይጠቀሳሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ የከበራ አጋጣሚ በተሳታፊዎቹ መካከል መቀራረብ እና ትውውቅ፣ መተሳሰብ እና አብሮነትን፣ ህብረትን እና የዓላማ አንድነትን ብሎም እስከ መተጫጨት እና በጋብቻ መጣመርን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

የከበሩ ንዋያቱን አጠቃቀም የተመለከተው ትንታኔም የወንድ እና ሴት እኩልነትን የሚያሳይ ነው፡፡ በዋቄፈናም ሆነ በገዳ ከበራ ላይ ወንድ ቦኩ፣ ወዴቻ፣ ከለቻ... ይዞ ሲገኝ ሴቷም ጫጩ፣ ጨሌ፣ ሲንቄ ይዛ መገኘቷ በእኩል ዓይን የመታየታቸው ወይም የእኩልነታቸው ማሳያ ነው፡፡ ከትዕምርቶቹም አቻዊነት አንፃር ለምሳሌ ከለቻ እና ጫጩ ጎን ለጎን የሚታዩ፣ አንዱ ከሌላው ጋር በአንድነት የሚገኙ ናቸው፣ “ከለቻ ባለበት ሁሉ የጫጩ መኖር የግድ ነው እንደዚሁም በባህል እና ወግ ስነስርዓት እና አከባበር ውስጥ የሚታይ ነው፡፡ አባወራ (ባል) ከለቻውን ይዞ ሲወጣ ባለቤቱ እንዲሁ ጫጩ በመያዝ ትወጣለች” (የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ 2000ዓ.ም፡ 232)፡፡ በዚህም ምክንያት ከለቻ የወንዶችን ክብር፣ ጫጩ ደግሞ የሴቶችን ክብር ይወክላሉ፡፡ በተመሳሳይ ቦኩ የአባ ቦኩ በትረ ሥልጣን የሆነውን ያህል፣ ሲንቄም የሀደ’ ሲንቄ በትረ ሥልጣን ናት፡፡

በተመሳሳይ ከለቻ በገዳ ሥርዓትም ሆነ በዋቄፈና እምነት ውስጥ ከለቻ ያለውን ክብር ሁሉ ጫጩም አለው፡፡ ይኸውም የወንድ እና የሴት መብት ብሎም የከበሩ ንዋያቱ ክብር በእኩል ሚዛን ላይ የተቀመጠ መሆኑን የሚያስገነዝብ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ሴቶች በገዳ ሥርዓት[38] ውስጥ ከሥርዓተ ፆታ አንፃር ፍትህን በመጠየቅ እንዲሁም ፍትህን በማስፈን ረገድ ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

[38] በገዳ ሥርዓት ውስጥ የሴቶች መብት እና እኩልነት የተከበረ ቢሆንም በኅብረተሰቡ ዘንድ ስለ ሴቶች ያለው ነባር እና የቆየ አመለካከት ሙሉ በሙሉ ተቀርፏል ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡

በቀረበው ገለፃ መሠረት ለጥናቱ መመልከቻነት የዋሉት ፅንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች የከበሩ ንዋያቱን ምንነት እና ትዕምርታዊ ፍቺ ለማሳየት ወሳኝ መሆናቸውን ነው፡፡ እነዚህ የከበሩ ንዋያት የሀገር በቀል እውቀት ውጤት ናቸው፤ የሚሰሩትም በሀገር በቀል እውቀት እና ልማድ ነው፡፡ ስለሆነም የህዝቡ እውቀት፣ ጥበብ እና ክሂሎት፣ የዓለም አተያይ መግለጫ ናቸው፡፡ በጥቅሉ ሲታይ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው እነዚህ እንስትነትን የሚያመለክቱት የከበሩ ንዋያት ባላቸው ትዕምርታዊ ፍቺ የሴቶችን ማህበራዊ ደረጃ እና ሚና፣ ክብር፣ ተቀባይነት እና ተደማጭነትን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ከትዕምርታዊ ፍቺ አንፃር ደግሞ እንስትነትን እና መራባትን የሚገልፁ ሲሆን ዕርቅ ለመፈፀም እና ግጭቶችን ለማስወገድ ጉልህ ድርሻ ያላቸው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በቱለማ ኦሮሞ ገዳ ሥርዓት ውስጥ እንስትነትን በተመለከቱ የከበሩ ንዋያት ላይ ትኩረት በማድረግ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ትዕምርት፣ ምልክት፣ ሀገር በቀል እውቀት፣ ሥርዓተ ከበራ የተሰኙ ፅንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች እንዲሁም ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት ስነዘዴዎች አገልግለዋል፡፡ እነዚህ የህዝቡን ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ሀብቶች የሚገልፁ ናቸው፡፡ የሥርዓተ ፆታ እሳቤንም አካተው ይዘዋል፡፡

ሰላም እና ዕርቅን ለመፍጠር፣ ግጭት እና ጦርነትን ለማስቀረት፣ ቤተሰባዊ እና ማኅበራዊ ደህንነትን ለማረጋገጥ፣ ማኅበራዊ ቀውሶችን ለመቀነስ ጉልህ ድርሻ እንዳላቸውም ጥናቱ ያመለክታል፡፡ ለዚህም እውነታ በጥናቱ ውስጥ የተተነተኑት ትዕምርቶች ጫጩ፣ ጨሌ፣ ሲንቄ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በተጓዳኝ የቀረቡት እንደ ኦኮሌ እና ጪጮ የመሳሰሉት የእንስቷን ባለሙያነት እና የዕደ ጥበብ ችሎታ የሚያሳዩ፣ የቱለማን ባህል እና ትውፊት የሚገልፁ ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱት እና የሀገር በቀል ዕውቀት ውጤት የሆኑት የከበሩ ንዋያት ለሥርዓተ ፆታ ግንዛቤ መዳበርም ሆነ ለሴቶች መብት መከበር እንዲሁም ለሰላም መስፈን የራሳቸው ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ ለሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም የሚበጁ አሰራሮችንም በውስጣቸው የያዙ ስለመሆናቸው መመስከር ይቻላል፡፡ የገዳ ሥርዓት እና የዋቄፈና እምነት ከነዚህ የከበሩ ንዋያት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ስለመሆኑም የጥናቱ ማጠቃለያ ይጠቁማል፡፡

## ይሁንታ

የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው በትንታኔው አፅንዖት የተሰጣቸው ጫጩ፣ ጨሌ፣ ሲንቄ የመሳሰሉት የከበሩ ንዋያት / Ulfaalee የሴቷን ክብር፣ ማህበራዊ ተቀባይነት እና ተደማጭነት ከፍ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ለሴቶች መብት መከበርም ሆነ ለሰላም ግንባታ የበኩላቸውን ጉልህ አስተዋፅዖ አላቸው፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት ሃሳቦች በምክረ ሃሳብ ደረጃ የጥናቱ ይሁንታ አካል ሆነው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

1. በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ የሚሰሩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የትዕምርቶቹን ፍቺ፣ ማህበራዊ ህጎች እና እሴቶች በማጥናት፣ ባህላዊውን አካሄድ ከዘመናዊው አሰራር ጋር በማዛመድ፣ በማዋሃድ፣ በማጎልበት፣ በማስተዋወቅ ተግባራዊ

ቢያደርጉ የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን እና የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማስፈን የሚያደርጉት ጥረታቸው ፍሬ ሊያፈራ፣ ተጨባጭ ውጤትም ሊያስገኝ ይችላል፡፡

2. ከዚሁ አንፃር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተስፋፋ ከመጣው ዘመናዊነትን እና የፋሽን መከተል አዝማሚያ የእንስትነት ትዕምርት የሆነውን ዛጎል (Eelellaa) ወንዶች ከተለያዩ አልባሳት ጋር በማሰራት ሲያጌጡበት ይስተዋላል፡፡ ጨጮ እና ሲንቄን መያዝ የማይገባቸው ያልተዳሩ ትናንሽ ታዳጊ ህፃናት እና ወጣቶች ሲጠቀሙ ይስተዋላል፡፡ ስለሆነም ይህ አይነቱ የፋሽን አጠቃቀም ባህላዊ ይዘቱን እንዳይለቅ ጥንቃቄ ማድረግ፣ ነባሩ ባህል እንደተጠበቀ እንዲዘልቅ ትኩረት መስጠት የግድ ይላል፡፡ የከበሩ ንዋያቱ ከአያት ቅድመ አያት በውርስ እና በቅርስነት ተላልፈው የመጡ ስለሆኑ ትውፊታዊነታቸው ሳይለወጥ እንዲዘልቁም ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ሀደ' ሲንቄዎች፣ አባ ገዳዎች እና የባህል እና ቱሪዝም ባለሙያዎች ተገቢውን ትምህርት መስጠት አለባቸው፡፡ እነዚህ የከበሩ ንዋያት ባህላዊ ይዘታቸው ሳይቀየር ተመዝግበው እንዲቀመጡ እና ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉም እራሱን የቻለ ሙዚየም ቢዘጋጅላቸው ለትምህርታዊ አገልግሎትም ሆነ ለገቢ ምንጭ ማስገኛ ሊውሉ ስለሚችሉ የተጠቀሱት አካላት ሊያስቡበት ይገባል። አዲሱ ትውልድም አያት ቅድመ አያቶቹ ትተውለት ያለፉትን የከበሩ ንዋያት፣ ትውፊት፣ ስነምግባር የከበራ ስነስርዓት… አተገባበር ሳይሸራርፍ መጠቀም እና ማስቀጠል ይጠበቅበታል፡፡

3. በሀገራችን የዓለም ዓቀፍ ሴቶች ቀን ማርች 8 በየዓመቱ ይከበራል፡፡ ነገር ግን ዓለም ዓቀፋዊው እሳቤ በተማሩ ጥቂት ልሂቃን ሴቶች ዘንድ እንጂ በገጠሪቷ ሴት ዘንድ ብዙም የሰረፀ አይመስልም፡፡ በገጠርም ብቻ ሳይሆን በከተማም ቢሆን ከኅብረተሰቡ ጋር ይልቁንም ፊደል ካልቆጠረችዋ ሴት ዘንድ እምብዛም የተዋሃደ፣ ተገቢውን ግንዛቤ ያላገኘ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ለአብዛኛዎቹ ሴቶች እንግዳ የሚሆነውን በዓል በተለይም በክልሉ ደረጃ "የሲንቄ በዓል" ብሎ በመሰየም ማክበር ይቻላል፡፡ ለዚህ ደግሞ መነሻ የሚሆን ልምድም አለ፡፡ ለምሳሌ በምሥራቅ ሸዋ ቦሰት ወረዳ የሲንቄ በዓል ሲከበር በመስክ በነበረን ቆይታ ተመልክተናል፡፡ ይህን ተሞክሮ ወደ ክልል ዓቀፍ ደረጃ መውሰድ ይቻላል፡፡ የሲንቄ ዓመታዊ በዓል ቢከበር ስለሲንቄ ምንነት፣ ስለ ሴቶች መብት እና እኩልነት በሀገርኛው አመለካከት ላይ ተመስርቶ ለመወያየትም ሆነ ጥሩ ግንዛቤ ለመፍጠር ያስችላል የሚል እምነት አለን፡፡ ከሥርዓተ ፆታ በተጓዳኝ የህዝቡንም አብሮ በሰላም የመኖር፣ የመከባበር እና የመደማመጥ ነባር እሴቶችን መጠበቅ፣ መንከባከብ፣ ማበልፀግ እና መጠቀም ወሳኝ የሆነበት ምዕራፍ ላይ የደረስንበት ጊዜ በመሆኑ የሴቶች ጉዳይ የሚመለከታቸው ተቋማትም ሆኑ መንግሥት በሙሉ ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡

# ዋቢዎች


ሕይወት ኢትዮጵያ (2008ዓ.ም.)፡፡ *ዖታዊነት እና ስነተዋልዶ ጤና*፡፡ አዲስ አበባ፣ Chora Printing Press.

ሙሉጌታ ነጋሣ (1997ዓ.ም)፡፡ "በአደኣ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴረጉማ ከግጭት አፈታት አንጻር"፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ (ያልታተመ)፡፡

ሰለሞን ተሾመ (2007 ዓ.ም)፡፡ ፎክሎር፡ ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ኃላ/የተ/የግ/ማህበር፡፡

ቀነዓ ለሚ (2010ዓ.ም)። የኦሮሞ ሚቶሎጂ ይዘታዊ ትንተና። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረበ፤ አአዩ: ለዶክትሬት ድግሪ ማሟያ (ያልታተመ)፡፡

ብሩ ጸጋዬ (2008 ዓ.ም)፡፡ **የሥልጣኔ** አፍሪካዊ ምንጭና በተረት መጋረጃዎች የተደበቁ እውነቶች፡፡ ኢትዮጵያ፣ አዳማ ድር ማተሚያ ቤት፡፡

ታቦር ዋሚ (2007 ዓ.ም)፡፡ የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች (ሦስተኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

እሸቱ ኢረና (2001 ዓ.ም)፡፡ የኦሮሞ ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

የኔዓለም አረዶ (2000 ዓ.ም)፡፡ "የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥናት (በኮኮሳና ገደብ ሀሰሳ ወረዳዎች)"፡ ፡ የማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993 ዓ.ም)፡፡ አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ (1998 ዓ.ም)፡፡ የኦሮሞ ታሪክ እስከ አሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፡ ፡ ሁለተኛ እትም፣ ፊንፊኔ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

_______(2000 ዓ.ም)፡፡ በገዳ ሥርዓት የቱለማ ኦሮሞ ፖለቲካ፡፡ የመጀመሪያ እትም፣ ፊንፊኔ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ያለው እንዳወቀ (2006 ዓ.ም)፡፡ የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር (3ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ ተፈራ ስዩም ማተሚ ቤት፡፡

ገናናው ከተማ (2014ዓ.ም)፡፡ "የቱለማ ኦሮሞ ገዳ ሥርዓት ተፈጥሯዊ እና ሰውሰራሽ የከበሩ ንዋያት ትዕምርታዊ ጥናት"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ በፎክሎር ለዶክትሬት ዲግሪማሟያ የተዘጋጀ፣ ያልታተመ፡፡

ጥላሁን ተሊላ (2007 ዓ.ም)፡፡ "የቱለማ ኦሮሞ "መርሣ" ወቅቶች ፎክሎር አውዳዊ ጥናት"፡፡ ያልታተመ፤ ለፎክሎር የፒ.ኤች.ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ ሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ ለፒ.ኤች.ዲ ማሟያ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ፈቃደ አዘዘ (1991ዓ.ም)፡፡ የሥነቃል መመሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም።

Blaxter Loraine. Hughes, Christina. Tight, Malcolm. (2006). How to Research. (Third edition) England, Open University press.

Bloor M. and Wood F. (2006). Key Words in Qualitative Method. London, SAGE publications.

Bruce S. and Yearley S (2006). The Sage Dictionary of Sociology. London, SAGE Publications.

Bruchac, Margaret M. (2014). Indigenous Knowladge and Traditiona Knowlage. United States, University of Pennsylania.

Charon, Joel M (1989). Symbolic interactionism. New Jersey, prentice hall.

Danesi, Marcel (2004). Messages, Sings, and Meanings; A Basic Textbook in Semiotics and Communication Theory (3edi). Toronto, Canadian Scholars Press.

Dirribii Damissee (2016). Ilaalcha Oromoo፡ Barroo Aadaa, Seenaa fi Amantaa Oromoo. Finfinnee.Saabaa publishing.

Dorson, M Richard (1972). Folklore and Folklife: An Introduction. Published by University of Chicago Press.

Ganaanaawu, Katamaa (2004). Qajeelfama Afoola Oromoo. Finfinnee. (Kan hin maxxanfamne).

Hooks, Bell (2015). Feminism is for everybody; Passionate politics. South End Press.

Hornbay AS. (2010). Oxford Advanced Leaner’s Dictionary. New York, Oxford University Press.

Jemila Adem (2014).“Women and Indigenious Conflict Resolution Institutions in Oromiya: Experience from Siinqee of the Wayyu Shanan Arsi Oromo in Adami Tullu Jiddu Kombolcha District of the Oromia National Regional State”.Addis Ababa University, College of Social Sciences.M.A Thisis.

Kuwee Kumsa (1997). “The Siiqqee Institution of Oromo Women”in Journal of Oromo Studies, vol. 4, Nos, Land 2, pp115-152.

Mack, Natasha. Woodsong Cynthia. Macqueen Kathleen M. Guest Greg. Namey Emily. (2005). Qualitative Research Methods: A Data Collector's Filed Guide. USA, Family Health International (FHI).

Mertens, Donna M. (2015). Research and Evaluation in Education and Psychology. (4th Edition) United States of America, SAGE publications.

Schechner, Richard (2015). Ritual and Performance. Cambrige: Cambrige University Press.

Taddesse Tamrat (1972). Church and State in Ethiopia 1270-1527. Oxford.

The World Bank (1998). Indigenous Knowledge Definations፡ Concepts and Applications.

UNEP (2008). Indigenous Knowledge in Disaster Management in Africa. Kenya.

Walliman, Nicholas (2006). Social Research Methods. London, Sage Publications.